፴፯፡ ይ. ሕ. ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ ነአምን ዕርገ ተከ ወዳግመ ምጽአተከ ንሴብሐከ ወንትአመነከ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ፡	፴፯፡ ይ.ሕ. አቤቱ ሞትህን ቅድስት ትንሣኤህንም እንነግራለን ፣ ዕርገትህን ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን፣ እና መሰግንሃለን እናምንሃለንም፣ ጌታችንና አምላካችን ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም ፡	37. *People*: We proclaim Your death, Lord, and your holy resurrection; we believe your ascension and your second advent. We glorify You, and confess You, we offer our prayer unto You and supplicate you, O our Lord and our God.
፴፰፡ ይ. ካ. ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ቃለ እግዚ አብሔር፣ ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወሠወሮ እምኔነ፡	፴፰፡ ይካ. ቃል ቀዳማዊ ነው፣ ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ያ ቃል ሥጋ ሆነ፡ በእኛም አደረ ከእኛም ሰወረው ፡	38. *Priest*: In the beginning was the Word, and that Word was the Word of God, and that Word was made flesh and dwelt among us, and His flesh hid him from us.
፴፱፡ ለብሰ ሥጋ ዘይማስን ወረሰዮ ዘኢይማስን ወበ ይእቲ ሥጋ ተቀሠፈ ዘኢይትቀሠፍ አምላክ፡	፴፱፡ የሚጠፋ ሥጋን ለበሰ፣ የማይጠፋም አደረገው፣ በዚህችም ሥጋ የማይገረፍ አምላክ ተገረፈ ፣	39. He put on mortal flesh and make it immortal, and through this flesh, God who can never be scourged, was scourged.
፵፡ ንዑ ትርአዩ ዘንተ ቅሥፈተ እለ ተሳተፉ ሕማመ ቢጽክሙ ወእለ ትትዋከፉ ሕማመ ፍቁራኒክሙ፣ ዕፁብ ውእቱ ለዘይሬእዮ በዓይን ወመድምም ውእቱ ለዘይሰምዖ በእዝን ፣ ንዑ ትርአዩ ጽፍዓተ መላ ትሕ እምገብር ወተኰርዖተ ርእስ በበትር በዐውደ ሊቃነ ካህናት፡	፵፡ በወንድማችሁ መከራ አንድ የምትሆኑ የወዳጆቻችሁንም መከራ የምትቀበሉ፣ ይህን ግርፋት ታዩ ዘንድ ኑ፣ በዓይን ለሚያየው ዕፁብ ነው፣ በጆሮው ለሚሰማው ድንቅ ነው፣ ከባሪያ የፊቱን መጸፋትና በሊቃነ ካህናቱም ሸንጎ ራስን በዘንግ መመታትን ታዩ ዘንድ ኑ፡	40. You, who are willing to partake of the suffering of your neighbours and to take upon yourselves the sufferings of your beloved ones, come to see this scourge. It is astonishing to him who looks at it with his eyes, and amazing to him who listen to it with his ears. Come to see the smiting on the cheeks by a servant and the beating on the head with sticks in the court of the chief priests.
፵፩፡ ንዑ ትርአዩ አክሊለ ዘሠክ ዘአስተቀጸልዎ ለማሕየዊ ኵሉ ዓለማት፡	፵፩፡ ሁሉን የሚያድን ጌታን ያቀዳጁትን የእሾህ ዘውድ ታዩ ዘንድ ኑ ፣	41. Come to see the crown of thorn with which they crowned the giver of life to all.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፵፪፡ ንዑ ናስተብርክ ለባሕቲቱ ኵልክሙ ሠራዊተ መላእክት እለ ትሠርሩ መልዕልተ አየራት ወእለ ትትፌነዉ ኀበ ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብት ወእለኒ ተዐርጉ ኀበ አብሕርት ወቀላያት፤	፵፪፡ ለርሱ ብቻ እንሰግድ ዘንድ ኑ፣ በአየር ላይ የምትወጡ ሁላችሁ የመላእክት ሠራዊት ወደ ፀሐይና ወደ ጨረቃ ወደ ከዋክብትም የምትላኩ፤ ወደ ባሕርና ወደ ቀላያትም የምትወጡ፣	42. Come to kneel to Him only all you the hosts of angels who fly above the air and who are sent towards the sun, the moon and the stars and who ascend to-wards the seas and lakes.[4]
፵፫፡ ባሕር ርዕደት ወማየ ተከዚ ጐየት ሶበ ርእየት ጽፍዓተ መላትሒሁ ለአምላክነ ፀሓይ ጸልመ ወወርኀ ደመወ ወከዋክብት እም ዕበየ ብርሃኖሙ ተዐርቁ፤	፵፫፡ የአምላክን የፊቱን መጸፋት ባየች ጊዜ ባሕር ተንቀጠቀጠች፣ ማየ ተከዚም ሸሸች፣ ፀሐይ ጨለመ ፣ ጨረቃም ደም ሆነ፣ ከዋክብትም ከብዙ ብርሃናቸው ተራቆቱ፤	43. The sea trembled and the waters of the stream fled when they saw God beaten on His cheeks; the sun was darkened, the moon became blood and the stars became void of their great light.
፵፬፡ ሞት ፈርሀ ወዲያብሎስ ወድቀ ወሲኦል ሖረት ምስለ እሊአሃ ኀቡረ ለቀበላ አምላክ ግሩም፤	፵፬፡ ሞት ፈራ፤ዲያብሎስም ወደቀ፣ ሲኦልም ግሩም የሆነ አምላክን ለመቀበል ከወገኖችዋ ጋራ በአንድ ነት ሄደች፤	44. Death was afraid, the Devil fell, and Hades went together with its own to receive the mighty God.
፵፭፡ ንዑ ትርአዩ ዕፀብ ነገረ ዘተገብረ ውስተ ቤተ ጸሎት ጊዜ ይበውእ ሊቀ ካህናት ውስተ ውሳጢተ መንጦላዕት ወይብልዋ ኵሎሙ ኀባኢተ መለኮት ይእቲ ወሠዋሪተ ኵሉ ሕሊናት፣ ቦአ ኀቤሃ እግዚአ አጋዕዝት ወመናፍስት እንዘ ይጼአን ዕዋለ አድግ ትሑት፣	፵፭፡ የካህናት አለቃ ወደ መጋረጃ ውስጥ በገባ ጊዜ በጸሎት ቤት የተደረገውን ድንቅ ነገር ታዩ ዘንድ ኑ፣ ሁሉም መለኮትን የምትሸሽግ ሕሊናትንም ሁሉ የምትሰውርናት ይሏታል፣ የአጋዕዝትና የመናፍስት ጌታ በተዋረደ አህያ ግልገል ተቀምጦ ወደርስዋ ገባ፤	45. Come to see the wonderful thing which was done in the house of prayer when the high priest entered within the veil of which all said that it was the dwelling place of the Deity and the con-cealing of all thoughts. The Lord of lords and spirits entered therein riding upon the lowly colt of an ass.
፵፮፡ መለኮቶ አርአየ ለኵሎሙ ሕፃናት እለ ይብሉ ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወቡሩክ አንተ እግዚአብሔር አምላከ አማልክት ወንጉሠ እስራኤል፤	፵፮፡ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ብሩክ ነው፣ አንተም የአማልክት አምላክ የእስራኤልም ንጉሥ እግዚአብሔር ብሩክ ነህ እያሉ ለሚያመሰግኑ ሕፃናት ሁሉ ጌትነቱን አሳየ ፤	46. He revealed his divinity to all the infants who said, Blessed is He who comes in the name of the Lord, and blessed are you, Lord, God of gods, and King of Israel.

[4] i.e. the waters above the firmament.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፵፯፤ ዑደተ ሖሣዕና አርአየ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ ቡሩክ በሉ እንዘ ትጸርሑ በዐቢይ ቃል ሖሣዕና በአርያም፤ ሖሣዕና በአርያም፤ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ይ. ሕ. ከማሁ እንዘ የዐውዱ፣	፵፯፤ የሖሣዕናን ዑደት ለነርሱ ለደቀ መዛሙርቱ አሳየ ብሩክ እርሱ በታላቅ ቃል እየጮኻችሁ ሖሣዕና በአርያም በሉ አላቸው፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም ፣ ይ.ሕ. እየዞሩ እንደዚሁ፤	47. He showed his disciples the manner of going around with the Hosanna; and the Blessed said unto them, Say, crying with a loud voice, hosanna in the highest. Hosanna in the highest, hosanna in the highest, hosanna in the highest. *People: The people shall repeat his words while going around.*
፵፰፤ ይ. ካ. እምሖሣዕናሁ አርአየ ተአምረ ወመንክረ ዘኢተገብረ እምቅድመዝ ወዘኢይከውን እምድኅረዝ፣ ሖሣዕና በአርያም፣ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ይ. ሕ. ከማሁ ፣	፵፰፤ ይ.ካ. ከመድኃኒትነቱ የተነሣ ከዚህ አስቀድሞ ያልተደረገ ከዚህም በኋላ የማይደረግ ተአምራትንና መንክራትን አሳየ፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም ፣ ይ.ሕ. እንደርሱ ፤	48. *Priest*: From his hosanna he showed miracles and wonders which have never been done before and will never happen again. Hosanna in the highest, hosanna in the highest, hosanna in the highest. *People: The people shall repeat his words.*
፵፱፤ ይ. ካ. እምሖሣዕናሁ አርአየ ጸጋ ወኃይለ ወሪዶ እምልዑል መንበሩ እንዘ ኢያንቀለቅል እመሠረተ ቤቱ፣ ሖሣዕና በአርያም ፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም ፣ ይ. ሕ. ከማሁ፤	፵፱፤ ይ.ካ. ከመድኃኒትነቱ የተነሣ ከቤቱ መሠረት ሳይናወጥ ከልዑል መንበሩ ወርዶ ጸጋንና ኃይልን አሳየ፣ ሖሣዕና በአርያም፣ሖሣዕና በአርያም ፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ይ.ሕ. እንደርሱ ፤	49. *Priest*: From his hosanna he showed grace and power, came down from his great throne without being moved from the foundation of his house. Hosanna in the highest, hosanna in the highest, hosanna in the highest. *People: The people shall repeat his words.*
፶፤ ይ. ካ. እምሖሣዕናሁ ወሀበ ፈልፈለ አንብዕ ለኃጥአን ከመ ያጽድቆሙ ለጊጉያን ያንጽሖሙ ለርሱሓን ወይሚጦሙ ለስሑታን፣ ሖሣዕና በአርያም ፣ ሖሣዕና በአርያም ፣ ሖሣዕና በአርያም፤	፶፤ ይ.ካ. ከመድኃኒትነቱ የተነሣ ለኃጥአን የዕንባ ምንጭ ሰጠ፣ የበደሉትን ያጸድቃቸው ዘንድ ፣ ያደፉትን ያነጻቸው ዘንድ ፣ የሳቱትን ይመልሳቸው ዘንድ፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም፣ ሖሣዕና በአርያም፣	50. *Priest*: From his hosanna he granted the sinners a spring of tears so that he may justify the wicked and purify the filthy and bring back those who sinned through ignorance. Hosanna in the highest, hosanna in the highest, hosanna in the highest.
፶፩፤ ይ. ካ. እምሖሣዕናሁ ጸገወ ብርሃነ ለዕውራን ዳግመ ዘኢይጠፍዕ ዘኢይክል ዓለም ነሢአቶ፤	፶፩፤ ይ.ካ ከመድኃኒትነቱ የተነሣ ለዕውራን፣ ዳግመኛ የማይጠፋ ዓለም ሊቀበለው የማይቻለው ብርሃንን ሰጣቸው፣	51. From His hosanna He granted the blind light which can not be extinguished again and which the world can not find.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፶፪፡ እምቅድመ ሕሊና የአምር ወእምቅድመ ሕሊና ይፈትን ወአልቦ ዘይትኀ ብአ፣	፶፪፡ ከሕሊና አስቀድሞ ያውቃል ከአሳብም በፊት ይመራምራል፣ የሚሰወረውም የለም፣	52. He knows before one thinks, examines before one thinks, and nothing is hidden from him.
፶፫፡ ይ. ዲ. በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ እገሌ ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ አባ ዕገሌ፣ አባ ቲቶ ወአባ ፊልሞና ወአባ እንድራኒቆስ ወአባ ባስሊቆስ፣ በእንተ እሉ አግብርቲከ አበዊነ ጳጳሳት ወአበዊነ ኤጲስቆጳሳት ወአበዊነ ካህናት ወአኃዊነ ዲያቆናት ርቱዓነ ሃይማኖት፣	፶፫፡ ይ.ዲ. ብፁዕ ንዑድ ቡሩክና ክቡር ስለሚሆን ስለ ጳጳሳችን አለቃ ስለ አባ ዕገሌ፣ ብፁዕ ስለ ሚሆን ስለ አባ ዕገሌ፣ ስለ አባ ቲቶ ፣ ስለ አባ ፊልሞና ፣ ስለ አባ እንድ ራኒቆስ ፣ ስለ አባ ባስሊ ቆስ፣ ባሮችህ ስለሚሆኑ ስለነዚህ አባቶቻችን ጳጳሳት፣ ስለ አባቶቻችን ኤጲስቆጳሳት ሃይማኖታ ቸው ስለቀና አባቶቻ ችን ካህናት ስለ ወንድሞ ቻችን ዲያቆናት ፤	53. *Deacon*: For the sake of the happy and blessed and honourable Patriarch Abba (.....) and the blessed Archbishop Abba (.....), Abba Titus, Abba Philemon, Abba Andronicus, Abba Basilicos. For the sake of your servants our fathers the orthodox archbishops, our fathers the bishops, our fathers the priests, our brothers the deacons.
፶፬፡ ወለእሉ ሕዝብከ መሐሮሙ ወለኵሎሙ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣሃሎሙ እወ እግዚኦ አምላክነ ኀድግ ሎሙ አበሳሆሙ ወኢትነጽር ምግባረ ኃጢአቶሙ፣እለ ይቀርቡኒ ለነሢአ ሥጋከ ቅዱስ ወለእለኒ ኢይቀርቡ ይቅረቡ አዝዞሙ በትእዛዘ ቃልከ ሁሉ ይነጽሕ፣	፶፬፡ እሊህንም ወገኖችህን ማራቸው፣ የሁሉንም ነፍስ አሳርፍ፣ይቅርም በላቸው፣ አቤቱ አምላካችን በደላቸውን በእውነት ይቅር በላቸው ፣ የኃጢአታቸውንም ሥራ አትመልከት፣ ቅዱስ ሥጋህን ለመቀበል የቀረቡትን፣ ያልቀረቡትንም ይቀርቡ ዘንድ እዘዛቸው ፣ በቃልህ ትእዛዝስ ሁሉ ይነጻል ፣	54. Have compassion upon these your people and rest the souls of them all and have mercy upon them, yea, Lord our God, forgive them their sins, do not look upon their sinful deeds, those who will draw nigh to receive your holy body, and those who will not draw nigh order them to draw nigh with the commandment of your work; and all of them will be clean.
፶፭፡ ለእሉኒ ወለኵሎሙ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣሃሎሙ ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወበእንተ እለ ተድኀሩ ውስተ ዛቲ እምነ ቤተ ክርስቲያን መሐሮሙ ውተሣሃሎሙ ለኵሎሙ ለዓለመ ዓለም፡፡	፶፭፡ የሊህንም የሁሉንም ነፍስ በአብርሃም በይስሐቅና በያዕቆብ አጠገብ አሳርፍ፣ ይቅርም በላቸው፣ ከዚህች ከእናታችን ቤተ ክርስቲያን ወደ ኋላ ያሉትን ሁሉንም ማራቸው፤ ይቅርም በላቸው ለዘለዓለሙ ፡፡	55. To these and to all grant rest to their souls and have mercy upon them in the bosom of Abraham, Isaac and Jacob; and these who have absented themselves from this church, our mother, pity them all and have mercy upon them, world without end.
* * *	* * *	* * *

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፶፮፡ ይ. ካ. ንፍቅ፡ ህየንተ ጸሎተ ቡራኬ ፡ ኦ ሥሉስ ቅዱስ አኃዜ ኵሉ ዓለም ዘገበርከ ዐቢየ ወመንክረ በሥልጣነ ቃልከ፡	፶፮፡ ይካ. ንፍቅ በጸሎተ ቡራኬ ፈንታ ፡ ልዩ ሦስት አቤቱ ዓለሙን ሁሉ የያዝህ፣ በቃልህ ሥልጣን ደገኛና ድንቅ ሥራን የሠራህ ፡	56. *The assistant priest shall say the following instead of the prayer of benediction*: O Holy Trinity, who holdest all the world, who have done great and wonderful deeds through the power of your word,
፶፯፡ ባርክ ምሥራቀ ወምዕራብ ሰሜነ ወደቡበ መስዐ ወአዜበ ፡ ባርክ ሰማየ ወምድረ ወባሕረ ወአፍላገ ወአንቅዕተ ማያት ወኵሉ ዓይነ ማይ፡	፶፯፡ ምሥራቁንና ምዕራቡን፣ ሰሜኑንና ደቡቡን፣ መስዐውንና አዜቡን ባርክ፣ ሰማይንና ምድርን ፡ ባሕሩንና ወንዞቹን፣ የውኃ ውንም ፈሳሾች የውኃውንም ምንጭ ሁሉ ባርክ ፡	57. bless the east and the west, the north and the south, the north east and the south east, (the north west and the south west), bless the heaven, the earth, the sea, the rivers, the source of water, and all the springs of water.
፶፰፡ ባርክ ነፋሳተ ሰማይ ወዝናማተ፣ ባርክ ፀሐየ ወወርኃ ወከዋክብተ ባርክ አድባረ ወአውግረ ዕፀወ ወሰብለ ወፍሬያተ ምድር፣	፶፰፡ የሰማይን ነፋስ ዝናሙንም ባርክ፣ ፀሐይንና ጨረቃን ከዋክብትንም ባርክ፣ ተራራውንና ኮረብታውንም፣ ዕንጨቱንና ሰብሉን፣ የምድርንም ፍሬ ባርክ፡	58. Bless the winds of the sky and the rains. Bless the sun, moon and stars. Bless the mountains and hills, the trees, herbs and the fruit of the earth.
፶፱፡ ባርክ እለ ሀለዉ በታሕተ ሰማይ ወእለሂ ሀለዉ በታሕተ ምድር ፡ ክርስቶስ አምላክነ ምላዕ ውስተ ልቦሙ ፈሪሆተ ስምከ ወአስተናብር ሕይወቶሙ እስከ ለዓለም፣ ቡራኬ ፫ተ ጊዜ ላዕለ ሕዝብ፡	፶፱፡ ከሰማይ በታች ያሉትን ከምድርም በታች ያሉትን ባርክ፣ አምላካችን ክርስቶስ ሆይ፣ በልቡና ቸው ስምህን መፍራትን ምላ፣ አነዋወራቸውንም እስከ ዘለዓለሙ አከናውን፣ ሦስት ጊዜ ሕዝቡን ይባርክ ፡	59. Bless those that are under heaven and those that are under earth. O Christ our God, fill their hearts with the fear of your name and make their lives to prosper forever. *Benediction over the people three times.*
፷፡ ይ. ዲ. ንፍቅ መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን፣	፷፡ ይ.ዲ. ንፍቅ አቤቱ የጳጳሳቱን አለቆች ጳጳሳቱንና ኤጲስቆጶሳቱን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን የክርስቲያንንም ወገኖች ሁሉ ማራቸው፣ይቅርም በላቸው ፡	60. *Asst. Deacon*: Lord, pity and have mercy upon the patriarchs, archbishops, bishops, priests, deacons and all the Christian people.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፷፩፤ ይ.ካ.ለእሉኒ ወለኵሎሙ አግብርቲከ ወአእማቲከ አዕርፍ ነፍሳተ አበዊ ሆሙ ወአበዊነ ጳጳሳት (ቅዱሳን)፣ አቡነ ጴጥሮስ ወአቡነ ጳውሎስ ወአቡነ ያዕቆብ ጳጳስ ወአቡነ ክቡር ጳጳስነ አባ ማቴ ዎስ፣ ዮሐንስ ወስምዖን ወያዕቆብ ወልደ እልፍ ዮስ ወያዕቆብ ሐዋርያ እኁሁ ለእግዚእነ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም፤	፷፩፤ ይ. ካ. የነዚህንም የሁሉ ንም የወንዶችና የሴቶች ባሮችህን የአባቶቻቸው ንና የቅዱሳን አባቶቻች ንን የጳጳሳቱን ነፍስ አሳርፍ፣ አባታችን ጴጥ ሮስና አባታችን ጳው ሎስ፣ አባታችን ጳጳሱ አባ ያዕቆብም ክቡር አባታ ችን ጳጳሱ አባ ማቴዎ ስም፣ ዮሐንስና ስምዖን የአልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም የኢየሩሳሌም ኤጲስቆጶስ የጌታችን ወንድም የሚ ሆን ሐዋርያው ያዕቆ ብም ፤	61. *Priest*: To those and to all your servants and your handmaids grant rest; to the souls of their fathers also and our fathers the holy bishops; our father Paul, and our father Peter, our father Abba James the bishop, and the honourable Bishop Abba Matthew. John, Simon and James the son of Alphaeus and James the Apostle, brother of our Lord and Bishop of Jerusalem.
፷፪፤ በእንተ እሉ አግብርቲከ ማርቆስ ወሉቃስ ቲቶ ፊልሞና ወቀሌምንጦስ ባስልዮስ ወአትናሲስ ወኤጲፋንዮስ ኤጲስቆ ጳስ ወአባ ሕርያቆስ ወአቡነ ክቡር ሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ ወብፁዕ ጳጳስነ አባ ሲኖዳ፣ ከመ ታሠኒ ሎሙ ሕይ ወቶሙ ወታዜኑ ወትረ መዓዛ ዕጣኖሙ ውት ምሐረነ ኪያነሂ በጸሎተ ዚአሆሙ ለዓለመ ዓለም፤	፷፪፤ ባሮችህ ስለሚሆኑ ስለ ማርቆስና ሉቃስ ቲቶ ፊልሞና ስለ ቀሌምንጦ ስም ባስልዮስና አትና ሲስ ኤጲፋንዮስና ኤጲ ስቆጶሱ አባ ሕርያቆስ፣ ክቡር የሚሆን ሊቀ ጳጳሱ አባ ዮሐንስ፣ አባታችን ጳጳሱ አባ ሲኖዳም፣ አነዋወራቸውን ታቀና ዘንድ ዘወትርም የዕጣ ናቸውን መዓዛ ታሻትት ዘንድ እኛንም በነርሱ ጸሎት ትምረን ዘንድ ለዘለዓለሙ ፤	62. For the sake of your servants Mark, Luke, Titus, Philemon, Clement, Basil, Athanasius, Epiphanius, and Abba Heryacos the bishop, and our honourable father the Patriarch Abba Youhannes, and our father Archbishop Abba Shenouda, beautify their lives and make the saviour of their incense unfailing and pity us through their prayers, world without end.
፷፫፤ መቅድመ አዕርፍ ነፍሳተ አበዊነ ጳጳሳት ወአበዊነ ኤጲስቆጶሳት እለ አዕ ረፉ ውስተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት ወዲያቆናት አናጉንስጢስ ወመዘምራን ወአፃውያነ ኀዋኀው ኀቡረ ፤ እስመ አንተ እግዚኦ ማዕምረ ኀቡአት አንሥ አሙ በትንሣኤከ ቅድ ስት፣	፷፫፤ አስቀድሞ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያረፉትን የአባ ቶቻችንን የጳጳሳቱንና ያባቶቻችንን የኤጲስ ቆጶሳቱን ነፍሳት የቀሳ ውስቱንና የዲያቆናቱን የአናጉንስጢስና የመዘ ምራኑንም፣ በር የሚዘ ጉትንም ነፍሳት በአንድ ነት አሳርፍ፣ አቤቱ አንተ የተሰወረውን የም ታውቅ ነህና በቅድስት ትንሣኤህ አስነሣቸው ፤	63. First rest the souls of our fathers the archbishops and our fathers the bishops who gained their rest in this church, the priests, deacons, anagonastis (readers) and singers together with the doorkeepers, because you, Lord, knows that which is hidden: raise them in your holy resurrection.
፷፬፤ ወለነኒ እለ ተጋባእነ ለነሢአ ሥጋከ ቅዱስ ወለሰትየ ደምከ ክቡር አቁመነ በየማንከ ምስለ እለ ገብሩ ፈቃደከ፣	፷፬፤ ቅዱስ ሥጋህን ለመቀ በልና ክቡር ደምህን ለመጠጣት የተሰበሰብን እኛንም ፈቃድህን ከሠሩ ሰዎች ጋር በቀኝህ አቁመን ፤	64. And cause us, who have gathered to take your holy body and drink your precious blood, to stand at your right hand with those who have fulfilled your will.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፷፭፤ አልሕቅ ሕፃናቲነ (ወወራ ዙቲነ) ወአንጎ መዋዕሊ ሆሙ እስከ ርስዓን ወኢታንዲ ብዑላኒነ ወአ ብዕል ነዳያኒነ፣ ፈውስ ድውያኒነ ወኢታድዊ ሕያዋኒነ ተሣሃል ዘሞተ ወመሐር ዘሐይወ ፣	፷፭፤ ሕፃናቶቻችንንና ጉልማ ሶቻችንን አሳድግ፣ ዕድሜ ያቸውንም አርዝም፣እስከ እርጅና ባለጸጎቻችንንም ድሆች አታድርግ፣ ድሆ ችንም ባለጸጎች አድርግ፣ ድውያኑን አድን፣ ሕያዋ ኑንም ጠብቅልን፣ የሞተ ውን ይቅር በል በሕይ ወት ያለውንም ማር ፤	65. Cause our children and our young men to grow and lengthen their days till old age, do not suffer our rich ones to be poor, enrich our poor, heal our sick, do not suffer our whole ones to be sick, have mercy upon the dead, and pity the living.
፷፮፤ ይ. ሕ. እግዚኦ መሐረነ እግዚኦ መሐከነ እግዚኦ ተሣሃለነ፣	፷፮፤ ይ.ሕ. አቤቱ ማረን፣ አቤቱ ራራልን፣ አቤቱ ይቅር በለን ፤	66. *People*: Lord have pity upon us, Lord spare us, Lord have mercy upon us.
፷፯፤ ይ. ካ. ባርክ ርእስየ ፣ ቡራኬ ላዕለ ኅብስት ፬ ጊዜ፣ ወቀድስ ነፍስየ ፣ ቡራኬ ላዕለ ጽዋዕ ፬ ጊዜ ፣ ወአንጽሕ ሥጋየ ፣ ቡራኬ ላዕለ ፪ሆሙ ፬ ጊዜ ፣ ለነሢአ ሥጋከ ማሕየዊ ወለሰትየ ደምከ ደመ ምሥጢር መለኮታዊ ፤	፷፯፤ ይ.ካ. ራሴን ባርክ ፣ ኅብስቱን ፬ ጊዜ ይባርክ፣ ነፍሴንም አክብር ፣ ደሙን ፬ ጊዜ ይባርክ ፣ ሥጋዬንም አንጻ፣ ፪ቱንም ፬ ጊዜ ይባርክ ፣ ማሕየዊ ሥጋህን ለመ ቀበል የመለኮታዊ ምሥ ጢር ደም የሆነ ደም ህንም ለመጠጣት ፤	67. *Priest*: Bless me (*benediction over the Host once*) and hallow my soul (*benediction over the cup once*), and purify my body (*benediction once more over both*) so that I may receive your life-giving body and drink your blood, the mysterious divine blood.
፷፰፤ ይ. ዲ. በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚብ ሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ ፤	፷፰፤ ይ.ዲ. በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔ ርን እንማልደው፣ ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድ ነት ይሰጠን ዘንድ ፣	68. *Deacon*: With all the heart let us beseech the Lord our God that He grant unto us the good communion of the Holy Spirit.
፷፱፤ ይ. ሕ. በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም፤	፷፱፤ ይ.ሕ. በፊት እንደ ነበረ ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጅ ይኖራል ፣	69. *People*: As it was, is and shall be unto generations of generations, world without end.
፸፤ በዝየ ይኅትም ሥጋ በደም ጠሚያ በአጽባ ዕቱ፣ ይ. ካ. ደሚረከ ተሀ በሙ ለኵሉሙ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ ይኩ ኖሙ ለሕይወት ወለ መድኃኒት ዘለዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን ፤	፸፤ በዚህ ጊዜ በጣቱ ጠምቶ በደሙ ሥጋውን ይቅባ፣ ይ.ካ. ከእርሱ ለሚቀበሉ ሰዎች አንድ አድርገህ ስጣቸው ፣ የዘለዓለም ሕይወት መድኃኒት ይሆ ናቸው ዘንድ፣ ይ.ሕ. አሜን ፣	70. *At this time he shall dip his finger into the blood and sign the body.* *Priest*: Grant it together unto them that take of it that it maybe unto them for life and salvation forever. *People*: Amen.
፸፩፤ ይ. ካ. ሀበነ ንኅበር በዘ ዚአከ መንፈስ ቅዱስ፣ ሀበነ ንንሣእ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ፣	፸፩፤ ይ.ካ. የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን፣ ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት እንድንቀበል አድርገን፣	71. *Priest*: Grant us to be united through your Holy Spirit and heal us by this oblation that we may live in you forever.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወ ይ ት ባ ረ ክ ስመ ስብሐቲሁ ለ ይ ኩ ን ለይኩን ቡሩክ ለይኩን ፡፡	የእግዚአብሔር ስም ምስጉን ነው ፤ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውም ምስጉን ነው ፤ የቸትነቱ ስም ይመስገን፣ ይሁን ይሁን የተመስገነ ይሁን ፡፡	Blessed is the name of Lord and blessed be he that comes in the name of the Lord, and Let the name of his glory be blessed so be it, so be it, so be it blessed.
፷፪፤ ይ. ሕ. ከማሁ ፣	፷፪፤ ይ.ሕ. እንደርሱ ፤	72. *People: The people shall repeat his words.*
፷፫፤ ይ. ካ. ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ ፤ ይ. ሕ. ከማሁ ፡፡	፷፫፤ ይ.ካ. የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክልን ፣ ይ.ሕ. እንደርሱ ፡፡	73. *Priest*: Send the grace of the Holy Spirit upon us. *People: The people shall repeat his words.*
* * *	* * *	* * *
፷፬፤ ይ. ዲ. ተንሥኡ ለጸሎት፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. ሰላም ለኵልክሙ፣ ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ፤	፷፬፤ ይ.ዲ. ለጸሎት ተነሡ ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን፣ ይ.ካ. ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ፣ ይ.ሕ. ከመንፈስህ ጋራ፤	74. *Deacon*: Stand up for prayer. *People*: Lord have mercy upon us. *Priest*: Peace be unto you all. *People*: And with your spirit.
፷፭፤ ይ. ካ. ጸሎተ ፈትቶ፣ እግዚአብሔር ዘተናገረ ምስለ አቡነ አብርሃም በላዕለ ዕፀ ምንባር እንዘ ይብል አብርሃም አብርሃም አብ ርሃም አነ ውእቱ አምላክከ ወአምላከ አበዊከ ወኢ ኮንኩ ባዕደ አምላከ፣	፷፭፤ ይካ. የመፈተት ጸሎት፣ ከአባታችን አብርሃም ጋራ በተቀመጠበት ዕንጨት ላይ እንዲህ ብሎ የተነጋገረ እግዚአብሔር፣ አብ ርሃም ሆይ፣ አብርሃም ሆይ፣ አብርሃም ሆይ፣ አምላክህና የአባቶችህ አምላክ እኔ ነኝ፣ ልዩ አምላክ አይደለሁም ብሎ፤	75. *Priest*: *Prayer of Fraction.* O Lord who spoke with our father Abraham, while he has sitting under the tree, saying, O Abraham, O Abraham, O Abraham, I am your God and your fathers' God, I am not a strange God.
፷፮፤ ወኩን ዐቃቤ ትእዛዝየ ወቃለ ዚአየ ዘነገርኩከ ወአነ እሁቦሙ ምድረ ለደቂቅከ ወአበዝኖሙ ለዘርዕከ ከመ ኮከበ ሰማይ ወከመ ኖፃ ዘድን ጋገ ባሕር ፣	፷፮፤ ትእዛዜን ፣ የነገርሁህ ንም ቃሌን የምትጠብቅ ሁን፣ እኔም ለልጆችህ ምድርን እሰጣቸዋለሁ፣ ዘርህንም እንደ ሰማይ ኮከብ እንደ ባሕር ዳር	76. Keep my commandment and my word which I have spoken to you and I will grant the earth to your children and multiply your seed like the stars of heaven and the sand of the sea.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፸፯፤ ተንሥእ ኦ አብርሃም ወንሣእ መሶበ ኅብስት ወጻሕበ ወይን ወግበር ሐፂነ ወፀተ እምደቂቅከ ምስሌከ ወዕርግ ዲበ ደብረ ታቦር ወጸውዖ ለካህን ዘስሙ መልከ ጼዴቅ ፫ተ ጊዜ እንዘ ትብል ኦ ብእሴ እግዚአብሔር ኦ ብእሴ እግዚአብሔር ኦ ብእሴ እግዚአብሔር፣ ወሶቤሃ ይወጽእ ብእሲ ዘመፍርህ ጥቀ ወሶበ ርኢኮ እንከ ኢትፍራህ ፤	፸፯፤ አብርሃም ሆይ ተነሥ፣ ኅብስት ያለበትን መሶብና ወይን ያለበትን ፊቀን መቀሊጭትም (መቀስ፣) አብጅ፣ ከብላቴኖችህም ሁለቱን ከአንተ ጋራ ይዘህ ወደ ተራራ ውጣ፣ ስሙ መልከ ጼዴቅ የሚባለውን ካህን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ብለህ ሦስት ጊዜ ጥሪው፣ ያን ጊዜ ፈጽሞ የሚያስፈራ ሰው ይወጣል፤ ባየኸውም ጊዜ አትፍራ ፤	77. Stand up, O Abraham, and take a platter of bread and a vial of wine, make a pair of scissors, take with you two of your household and mount the mountain and call the priest who is called Melchisedec, call him three times saying, O man of God, O man of God, O man of God. At that time there will come a wonderful man; when you see him do not be afraid.
፸፰፤ ወተንሥአ አብርሃም በከመ ነበቦ እግዚአብሔር ወነሥአ ምስሌሁ መሶበ ኅብስት ወጻሕበ ወይን ወክልኤተ እምደቂቁ ፤ ወገብረ ሐፂነ ወዐርገ ዲበ ደብረ ታቦር ወጸርሐ እንዘ ይብል ኦ ብእሴ እግዚአብሔር ኦ ብእሴ እግዚአብሔር ኦ ብእሴ እግዚአብሔር ፃእ፣ ወእምዝ ይወፅእ ብእሲ ዘመፍርህ በሕቁ ወሶበ ርእዮ አብርሃም ወድቀ በገጹ ወኮነ ከመ ምውት፣	፸፰፤ አብርሃምም ተነሣ፣ እግዚአብሔር እንደ ነገረው ኅብስት ያለበትን መሶቡንና ወይን ያለበትን ፊቀኑን ከብላቴኖቹም ሁለቱን ይዞ መቀሊጭቱንም አበጀ፤ ወደ ተራራም ወጣ፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ውጣ ብሎም ጮኸ ከዚህ በኋላ ፈጽሞ የሚያስፈራ ሰው ወጣ፣ አብርሃምም ባየው ጊዜ በግንባሩ ወደቀ፣ እንደ ሞተም ሆነ ፤	78. Abraham stood up as God told him and took with him a platter of bread, a vial of wine and two of his household. He made a pair of scissors, mounted the mountain and cried out saying, O man of God, O man of God, O man of God, come out. Then a very wonderour man came out, and when Abraham saw him he fell on his face and became like a dead man.
፸፱፤ ወሰፍሐ እዴሁ መልከ ጼዴቅ ወአንሥአ ወይቤሎ ተንሥእ ኦ አብርሃም ወኢትፍራህ እስመ እግዚአብሔር ዘፈነወከ ኀቤየ ውእቱ ይቤለኒ ይመጽእ ኀቤከ፤	፸፱፤ መልከጼዴቅም እጁን ዘርግቶ አነሣው፣ አብርሃም ሆይ ተነሥ አትፍራ አለው፣ ወደኔ የላከህ እግዚአብሔር እርሱ ወዳንተ ይመጣል ብሎ ነግሮኛልና ፤	79. And Melchisedec stretched forth his hands and raised him saying: Stand up, O Abraham, and do not be afraid because God who sent you unto me told me that you would come unto me.
፹፤ ወተንሥአ አብርሃም ወተናገሩ ፪ሆሙ ዕበየ ቲሁ ለእግዚአብሔር አምላክነ ፤	፹፤ አብርሃምም ተነሣ ፣ ሁለቱም የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ጌትነቱን ተነጋገሩ ፤	80. And Abraham stood up, and both spoke together about the greatness of the Lord our God.
፹፩፤ ይ. ዲ. ጸልዩ ፣ ይ. ሕ. አቡነ ዘበሰማያት፤	፹፩፤ ይ.ዲ. ጸልዩ ፣ ይሕ. አቡነ ዘበሰማያት፣ (ቅዳ. ሐዋ. ቍ. ፷)	81. *Deacon*: You pray. *People*: Our father who are in heaven (Anaphora of the Apostles No. 60).

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፹፪፡ ይ. ካ. ወተንሥአ አብርሃም ወነሥአ መቅረፀ ወቀረፀ አጽፋረ እደዊሁ ወእገሪሁ ወሥእርተ ርእሱ፡ ወተንሥአ መልከጼዴቅ ወነሥአ መሶበ ኅብስት ወጻሕበ ወይን ወአንሥአ አዕይንቲሁ ውስተ ሰማይ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወቀደሰ ወወሀበሙ በረከተ ለአብርሃም ወለደቂቁ፡	፹፪፡ይ.ካ. አብርሃምም ተነሥቶ መቀሊፎቱን ይዞ የእጁንና የእግሩን ጥፍሮች ቈረጠ፣ የራሱንም ጠጉር ፣ መልከጼዴቅም ተነሥቶ ኅብስት ያለበት መሶቡንና ወይን ያለበት ፈቀኑን ይዞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አንሥቶ አመሰገነ፣ ባረከ ቈረሰም፣ ለአብርሃምና ለልጆቹ በረከትን ሰጣቸው፡	82. *Priest*: Abraham stood up and took a pair of scissors and cut the nails of his hands and feet and the hair of his head. Melchisedec stood up and took the platter of bread and the vial of wine and raised his eyes towards heaven, gave thanks, blessed and broke and granted blessing to Abraham and his household.
፹፫፡ ኦ እግዚአብሔር (አምላክነ) ዘተወከፍከ ቍርባነ ዝኩ ጻድቅ ተወከፍ ኀቤከ ዘንተ መሥዋዕ ተነ ወአንጽሐነ በፍጹም ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ ወሕሊና ከመ በልብ (ንጹሕ) ወበፍርሃተ ነፍስ ንንብብ ዘእንበለ ጽርዓት ወኢፍርሃት ወከመ ንበል ኦ እግዚ አብሔር አብ ቅዱስ አቡነ ዘበሰማያት ፡	፹፫፡ የዚህን ጻድቅ ቍርባን የተቀበልህ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ይህን መሥዋዕታችንን ወዳጅተ ተቀበል፣ በፍጹም ነፍስና ሥጋ በመንፈስና በሕሊና አንጻን፣ በንጹሕ ልብና በነፍስ ፍርሃት ያለማቋረጥና ያለመፍራት እንናገር ዘንድ፣ በሰማይ ያለህ ቅዱስ አባታችን እግዚአብሔር ሆይ ብለንም እንጠራ ዘንድ፡	83. O Lord our God, who did accept the offering of this righteous one, accept this our sacrifice and purify us completely, soul, body, spirit and mind, so that, with pure heart and fear of soul, we may speak continually without fear and say, O holy God: Our Father who are in heaven,
፹፬፡ ይ. ካ. ናስተበቍዕከ ኦ አብ ቅዱስ ወኔር ዘያፈቅር ኂሩተ፡ ኢታብአነ ውስተ መንሱት ወኢይቅንየነ ስሕተት አላ አድኅነነ እምኩሉ ምግባረ እኩይ ወእምሕሊናሁ ወጽርዓታቲሁ ወመናግንቲሁ ወሁከታቲሁ፡	፹፬፡ ይ.ካ. ቅዱስ አባት ሆይ፣ ቸርነትንም የምት ወድ ቸር ሆይ፣ እንማልድሃለን፣ ወደ ጥፋት እንዳታገባን፡ ስሕተትም እንዳይገዛን ከክፉ ሥራ ሁሉ አድነን እንጂ ከአሳቡ ከቦዘኑ ከተንኮሉ ከሁከቱም ፡	84. We beseech you, O holy kind Father, lover of good, lead us not into temptation, let not sin have dominion over us, but deliver us from every evil deed and from its thought and its opposition and its deceit and trouble.
፹፭፡ ወአብጥሎ ለዘያሜክረነ ወስድዶ እምኔነ ወገሥጽ ሁከታቲሁ ዘተከለ ዲቤነ ወብትክ እምኔነ ምክንያተ እንተ ትወስደነ ውስተ ኃጢአት ወባልሐነ በኃይልከ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ፡	፹፭፡ የሚፈታተነንን አጥፋው፣ ከእኛም አርቀው ፣ በእኛ ላይ የተከለውን ሁከቱንም ገሥጽ፣ ወደ ኃጢአት የምትወስደንንም ምክንያት ከእኛ ቍረጥ፣ ጽኑ በሚሆን ኃይልህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አድነን ፡	85. Destroy our tempter, send him away from us, and rebuke the trouble which he planted into us, uproot from us the motives which thrust us into sin, and deliver us with Your holy power through Jesus Christ our Lord.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፹፮፤ ይ. ሕ. ሠራዊተ መላ እክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም፣ ወይኬልልዎ ለመድኃኔ ዓለም ሥጋሁ ወደሙ ለመድኃኔ ዓለም ፣ ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ለመድኃኔ ዓለም በአሚነ ዚአሁ ለክርስቶስ ንገኒ ፤	፹፮፤ ይ.ሕ. የመድኃኔ ዓለም የመላእክት ሠራዊት በመ ድኃኔ ዓለም ፊት ይቆ ማሉ፣ መድኃኔ ዓለምን ያመ ሰግኑታል ፣ የመድኃኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ ይህ ነው፣ ወደ መድኃኔ ዓለም ፊት እንቅረብ፣ እርሱን በማ መን ለክርስቶስ እንገ ዛለን ፤	86. *People*: The hosts of the angels of the Saviour of the world stand before the Saviour of the world. They encircle the Saviour of the world, even the body and blood of the Saviour of the world. Let us draw near the face of the Saviour of the world. In the faith which is of him let us submit ourselves to Christ.
፹፯፤ ይ. ዲ. ንፍቅ፤ አርኃዉ ኖኃተ መኪንንት	፹፯፤ ይ.ዲ. ንፍቅ መኳንንት ደጆችን ክፈቱ ፤	87. *Asst. Deacon*: You princes open the gates.
፹፰፤ ይ. ዲ. እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ ፤	፹፰፤ ይ.ዲ. የቆማችሁ ሰዎች ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድ ርጉ ፤	88. *Deacon*: You, who are standing, bow your heads.
፹፱፤ ይ. ካ. መልዐ ሀብታተ ጸጋ ወልድከ ዋሕድ፤ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክር ስቶስ ወአመነ በሕማሙ ማሕየዊ ወዜነወነ ሞቶ ወአመነ በትንሣኤሁ በፍ ጹም ምሥጢር ፤	፹፱፤ ይ.ካ. ያንድ ልጅህ የጌታ ችን የአምላካችንና የመ ድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የጸጋው ሀብት መላ ፣ ማሕየዊ በሚሆን ሕማሙ አምነናል፤ ሞቱን ተናገርን፣ በፍጹም ምሥ ጢር መነሣቱንም አምነ ናል፤	89. *Priest*: The gift[5] of the grace of Your only-begotten Son, our Lord and our God and our Saviour Jesus Christ has been completed. We have believed in His life-giving sufferings and proclaimed His death and believed His resurrection in a perfect mystery.
፺፤ ይ. ዲ. ስግዱ ለእግዚአ ብሔር በፍርሃት ፤ ይ. ሕ. ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ ፤	፺፤ ይ.ዲ. በፍርሃት ሁናችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ ፤ ይ.ሕ. አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን፣ እናመሰግንሃለንም፤	90. *Deacon*: Worship the Lord with fear. *People*: Before You, Lord, we worship and we do glorify You.
፺፩፤ ይ. ካ. ጸሎተ ንስሓ ፤	፺፩፤ ይ.ካ. ጸሎተ ንስሐ ፤ (ቅዳ. ሐዋ. ቍ. ፹፪-፹፰)፤	91. *Priest*: Prayer of Penitence. (*Anaphora of the Apostles* 72-88).
፺፪፤ ይ. ዲ. ነጽር ፤	፺፪፤ ይ.ዲ. ተመልከት ፤	92. *Deacon*: Give heed.
፺፫፤ ይ. ካ. ቅድሳት ለቅዱሳን፣ ይ. ሕ. ፩ አብ ቅዱስ፣ ፩ ወልድ ቅዱስ፣ ፩ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ፤	፺፫፤ ይ.ካ. ቅድሳት ለቅዱሳን ፤ ይ.ሕ. ቅዱስ አብ አንድ ነው ፤ ቅዱስ ወልድ አንድ ነው ፤ መንፈስ ቅዱስም አንድ ነው ፤	93. *Priest*: Holy things for the holy. *People*: One is the Holy Father, one is the Holy Son, one is the Holy Spirit.
፺፬፤ ይ. ካ. እግዚአብሔር ምስለ ኩልክሙ፣ ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ ፤	፺፬፤ ይ.ካ. እግዚአብሔር ከሁላ ችሁ ጋር ይሁን ፤ ይ.ሕ. ከመንፈስህ ጋራ፤	94. *Priest*: The Lord be with you all. *People*: And with your spirit.

[5] i.e. the Holy Communion.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፺፭፡ ወእምዝ ያንሥእ ካህን ኅብስተ ፍጹመ በእደሁ ወይበል እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ፫ተ ጊዜ በልዑል ዜማ፣ ፲ወ፭ተ ጊዜ በንኡስ ዜማ፡ ይ. ሕ. ከማሁ ፣ ወእምዝ ይ. ካ. ፫ተ ጊዜ ይ. ሕ. ፪ተ ጊዜ ፡	፺፭፡ ከዚህም በኋላ ቁሱ መላውን ኅብስት በእጁ ይዞ ያዖሃ፣ እንዲህም ይበል ፣ አቤቱ ክርስቶስ ማረን ፫ ጊዜ በከፍተኛ ዜማ፣ ፲፭ ጊዜም በንዑስ ዜማ ፣ ይ.ሕ. እንደርሱ ፣ ከዚህ በኋላ፡ ይ.ካ. ፫ ጊዜ ይ.ሕ. ፪ ጊዜ ፡	95. *The priest shall then lift up the whole Host with his hand and say*: O Lord Christ, have compassion upon us. *(three times in a loud chant and fifteen times in a low chant).* *The people shall repeat his words.* *Then the priest shall repeat them three times and the people twice.*
፺፮፡ ይ. ዲ. እለ ውስተ ንስሓ ሀለውክሙ አትሕቱ ርእሰ ክሙ፡	፺፮፡ ይ.ዲ. በንስሓ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ ፡	96. *Deacon*: You, that are penitent, bow your heads,
፺፯፡ ወእምዝ ተመይጦ መን ገለ ሕዝብ ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር አምላክነ ፡፡ * * * ፺፰፡ ወእምድኅረ ተመጠዉ ፣ ይ. ካ. ኅዳፈ ነፍስ ፡ ወካዕበ ናስተበቍዖ ለዘ ኵሉ ይእኅዝ እግዚአ ብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክር ስቶስ ፡	፺፯፡ ከዚህ በኋላ ወደ ሕዝቡ ተመልሶ፣ ይ.ካ. አምላካችን እግዚአብ ሔር ሆይ (ቅ.ሐ.ቍ.፺፭-፻፳፮)፣ * * * ፺፰፡ ከተቀበሉም በኋላ ፣ ይ.ካ. ኅዳፈ ነፍስ፣ ዳግመኛ ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታ ችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔር አብን እንማልዳለን ፡	97. *Then he shall turn to the people and say*: Lord our God ... (*Anaphora of the Apostles* 95-126). * * * 98. *After receiving the Holly Communion*: *Priest*: *Pilot of the soul*: Again we supplicate God the Almighty, Father of our Lord and our Saviour Jesus Christ:
፺፱፡ ኦ ዘአፍቀርከ ትሕ ትናሁ ለዕጓለእመሕያው እምዕበዮሙ ለመላእክት፣ ኦ ዘአፍቀርከ ንዴተ ዚአሁ ለአዳም እመዛግብ ቲሆሙ ለነገደ አብርሃም ፡	፺፱፡ ከመላእክት ገናንነት ይልቅ የሰውን ትሕትና የወደድህ ከነገደ አብርሃም መዛግ ብት ይልቅ የአዳምን ንዴት የወደድህ አቤቱ፡	99. O You who did love the humility of man more than the greatness of angels, O You who did love the poverty of Adam more than the treasuries of the tribe of Abraham.
፻፡ ኦ ዘፈተውከ ሥነ ላህዩ ለዳዊት እመልክዐ ገጹ ለኤልያብ ወልደ ኢያቡሳ ዊት ፣ ኦ ዘለከ አፍቅሮተ ሰብእ እንዘ አምላክ አንተ እግዚብሔር አምላክነ ፡	፻፡ ከኢያቡሳዊት ልጅ ከኤልያብ ፊት መልክ ይልቅ የዳዊትን የመልኩን ደም ግባት የወደድህ ሆይ፣ አምላክ ስትሆን ሰውን መውደድ ያለህ አምላካ ችን እግዚአብሔር ሆይ፡	100. O You who did love the beauty of David more than the beauty of Eliab the son of the Jebusite. O You who did love man while You are God, you are the Lord our God.
፻፩፡ ይ. ዲ. ጸልዩ ፡	፻፩፡ ይ.ዲ. ጸልዩ ፣	101. *Deacon*: You pray.
፻፪፡ ይ. ካ. ኅድፍ ነፍሰነ ወሥጋነ ኦ ኅዳፈ፣ኦ አምላክ መስተሣህል አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክር ስቶስ ፡	፻፪፡ ይ.ካ. የምታነጻ ሆይ ሥጋችንንና ነፍሳችንን አንጻ ፣ የጌታችንና የመድ ኃኒታችን የኢየሱስ ክርስ ቶስ አባት፡ ይቅር ባይ አምላክ ሆይ ፡	102. *Priest*: O purifier, purify our souls and bodies, O merciful God, Father of our Lord and our Saviour Jesus Christ.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፻፫ ፤ ቶሳሕከ ማየ ምስለ ወይን፣ ነፋሰ ምስለ እሳት፤ ወማየሂ ዘምስለ መሬት ከማሁ ቶስሕ ድካመ ዚአነ ውስተ ጽንዐ መለኮትከ፣ ወደምር ካዕበ ሕማመ ዚአነ ውስተ ሕማመ መስቀልከ ፤	፻፫ ፤ ውኃን ከወይን ጋራ ቀላ ቀልህ፣ ነፋስንም ከእሳት ጋራ ውኃውንም ከመሬት ጋራ ቀላቀልህ፣ እንዲሁ የእኛን ድካም ከመለኮትህ ጽንዕ ጋራ ጨምር፣ ዳግመኛም የእኛን መከራ ከመስቀልህ መከራ ጋራ አንድ አድርግ፤	103. You did mix water with wine, wind with fire, water with earth; likewise unite our weakness with the power of your divinity. Unite also our sufferings with the sufferings of your cross.
፻፬ ፤ ኀቤከ ንስእል ኀቤከ ናስተ በቍዕ ኀቤከ ንትመሀ ለል ለዓለመ ዓለም ፤ ይ. ሕ. አሜን ፤	፻፬ ፤ ወዳንተ እንለምናለን ወዳ ንተ እንማልዳለን፣ ወዳንተ እንማለላለን ለዘለዓለሙ፣ ይ.ሕ. አሜን ፤	104. Unto You we offer our prayers, we supplicate You and we intreat You, world without end. *People*: Amen.
* * *	* * *	* * *
፻፭ ፤ ይ. ካ. አንብሮ እድ ፤ እግዚአብሔር አምላክነ ባርክ አግብርቲከ ወአ እማቲከ እለ ፃመዉ ወመጽኡ ቤተ መቅደስከ ኀበ የኀድር ብዕለ ስብሐ ቲከ ፤ ባርክ እደ ወአን ስተ አዕሩገ ወሕፃናተ፤	፻፭ ፤ ይ.ካ. አንብሮ እድ አም ላካችን እግዚአብሔር የጌትነትህ ብዕል ወደ ሚያድርበት ቤተ መቅደ ስህ ደክመው የመጡትን አገልጋዮችህን ባርክ ፤ ወ ን ዶ ቹ ን ና ሴቶቹን ሽማግሌዎቹንና ሕፃናቱን ባርክ ፤	105. *Priest*: *The laying on of the Hand.* Lord our God, bless your servants and your handmaids who have taken the trouble to come to your sanctuary in which the greatness of your glory dwells. Bless men and women, old and babes.
፻፮ ፤ ወኪያነሂ ደምር በኃይለ መላእክቲከ ቅዱሳን ወክ ድነነ በመንጦላዕተ ብር ሃንከ ፤ ወሠውረነ በዕፀ መስቀልከ፣ ወአግኀሠነ እምኵሉ ምግባረ እኩይ፤	፻፮ ፤ እኛንም በቅዱሳን መላ እክትህ ኃይል አንድ አድርግ፣ በብርሃንህ መጋ ረጃ ጋርደን ፤ በዕፀ መስቀልህም ሰውረን፣ ከክፉ ሥራም ሁሉ አርቀን ፤	106. Unite us with the power of Your holy angels, cover us with the curtain of Your light, hide us with the tree of Your cross and keep us apart from every evil deed.
፻፯ ፤ ወአኀድረነ ውስተ ማኀ በሮሙ ለቅዱሳን እለ ያዐርጉ ጸሎተ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት እለ በላዕነ ሥጋከ ወእለ ሰተይነ ደመከ ይኩነነ ለሥርየተ ኃጢአት ወለ ሕይወት ዘለዓለም፣በፈዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወ ዘ ል ፈ ኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፤	፻፯ ፤ በጊዜው ሁሉና በሰዓቱ ሁሉ ጸሎትን ከሚያሳ ርጉ ቅዱሳን መላእክት ማኀበር ውስጥ አሳድረን፣ የበላነው ሥጋህ የጠጣ ነውም ደምህ ለኃጢአት ማስተሥረያና ለዘለዓለም ሕይወት ይሁነን፣ ባንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን ፤	107. Make us to dwell in the congregation of the saints who offer up prayer at every time and every hour; and to us who have eaten your body and drunk your blood: let them be for the remission of sin and for eternal life, through your only-begotten Son through whom to You with him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.
* * *	* * *	* * *

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ	**የኤጲፋንዮስ ቅዳሴ**	***THE ANAPHORA OF ST. EPIPHANIUS*** [1]
፩፡ አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ኤጲፋንዮስ ኤጲስቆጶስ ዘደሴተ ቆጵሮስ፡ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳ ቲነ አባ ዕገሌ ወምስለ ሊቀ ጳጳስነ አባ ዕገሌ ወምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ወይዕቀባ ለሀገ ሪትነ ኢትዮጵያ ለዓለመ ዓለም አሜን፡	፩፡ የቆጵሮስ ደሴት ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የተናገረው የቍርባን ምስ ጋና፡ ጸሎቱና በረከቱ ከጳጳሳቱ አለቃ አባ ዕገሌና ከጳጳ ሳችን አባ ዕገሌ ከሁላችንም ጋራ ይኑር፡ ሀገራችን ኢትዮጵያንም ይጠብቃት ፡ ለዘለዓለሙ አሜን ፡	1. The Anaphora of St. Epiphanius,[2] Bishop of the Island of Cyprus. May his prayer and blessing be with our Patriarch, our bishop all Christian people and our country Ethiopia, world without end. Amen.
፪፡ ይ. ካ. እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ፡ ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ፡ ይ.ካ. አእኵትዎ ለአምላ ክነ፡ ይ. ሕ. ርቱዕ ይደሉ፡ ይ. ካ. አልዕሉ አልባቢ ክሙ፡ ይ. ሕ. ብነ ኀበ እግዚአ ብሔር አምላክነ ፡	፪፡ ይ.ካ. እግዚአብሔር ከሁላ ችሁ ጋራ ይሁን ፡ ይ.ሕ. ከመንፈስህ ጋራ ፡ ይ.ካ. አምላካችንን አመስ ግኑት ፡ ይ.ሕ. እውነት ነው ይገባል ፡ ይ.ካ. ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ ፡ ይ.ሕ. በአምላካችን በእግ ዚአብሔር ዘንድ አለን ፡	2. *Priest*: The Lord be with you all. *People*: And with your spirit. *Priest*: You give thanks unto our God. *People*: It is right, it is just. *Priest*: Lift up your hearts. *People*: We have lifted them up unto the Lord our God.
፫፡ ይ. ካ. ዐቢይ ውእቱ እግዚአብሔር በዕበዩ ቅዱስ በቅዳሴሁ፡ እኵት በአኰ ቴቱ፡ ወስቡሕ በስብሐ ቲሁ፡ ቀዳማዊ ውእቱ ዘኢይብልዎ እማእዜ፡ ወማዕከላዊ ውእቱ ዘኢይ ብልዎ እስከ ይእዜ ወደ ኃራዊ ውእቱ ዘኢይብ ልዎ እስከ ዝየ፡	፫፡ ይ.ካ. እግዚአብሔር በገና ንነቱ ገናና ነው፡ በቅድስ ናው የተቀደሰ ነው፡ በም ስጋናው የተመሰገነ ነው፡ በክብሩም የከበረ ነው፡ ከመቼ ወዲህ የማይሉት ቀዳማዊ ነው፡ እስከ ዛሬ የማይሉት ማዕከላዊ ነው፡ እስከዚህ የማይሉትም ደኃራዊ ነው ፡	3. *Priest*: God is great in his greatness, holy in his holiness, blessed in his beatitude and glorified in his glory. He is the first – yet of him it is not said: "When was his beginning?" with him it is ever "now" – yet of him it is not said: "How long will he undure?" and he is the last – yet of him it is not said: "At what time will his end be?"

[1] This Anaphora is celebrated on the following occasions:
a) On 17th Ginbot (Bashans – May) the memerial day of the death of St. Epiphanius.
b) On the fast day of days of Epiphany.
c) On Great Thursday (that is, the Thursday next before Easter).
d) During the rainy season.

[2] He was born in 315 at Bezanduca, a small village in Palestine, of Jewish parents. After having been converted and become a Christian , he went to Egypt and spent a long time in its monasteries. On his return to Palestine, he was ordained priest by the Bishop of Eleutherapolis and became the abbot of a monastery which he founded near his native place. In 367 he was consecrated Bishop of Cyprus – an office which he held till his death on 17th Ginbot (May) 402 A.D.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፬፤ አልቦ ጥንት ለሀላዊሁ፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለክዋኔሁ፤ አልቦ ጕልቍ ለመዋዕሊሁ፤ ወአልቦ ሐሳብ ለዓመታቲሁ፤ ወአልቦ ርስዓን ለውርዛዊሁ፤ ወአልቦ ድካም ለጽንዐ ኃይሉ፤ አልቦ ሙስና ለመልክኡ ወአልቦ ጽልመት ለብርሃነ ገጹ ፤	፬፤ ለአነዋወሩ ጥንት የለውም ፤ ለአኳኋኑም ፍጻሜ የለውም፤ ለዘመኑ ቍጥር የለውም፤ ለዓመታቱም ልክ ቍጥር የለውም፤ ለውርዝውናው ማርጀት የለበትም፤ ለኃይሉም ጽናት፤ ድካም የለበትም፤ ለመልኩ ጥፋት የለበትም፤ ለፊቱ ብርሃንም ጨለማ የለበትም ፤	4. There is no beginning of his being, there is no end of his existence, his days are numberless and his years are countless. His youth does not wax old, the strength of his power does not become weary, his countenance is incorruptible and the light of his face can not be darkened.
፭፤ አልቦ ድንጋግ ለባሕረ ጥበቡ ወአልቦ መስፈርት ለሣህለ ትእዛዙ አልቦ ዐቅም ለስፍሐ መንግሥቱ ወአልቦ ወሰን ለራኅበ ምኵናኑ፤	፭፤ ለጥበቡ ባሕር ድንበር የለውም፤ ለትእዛዙም ይቅርታ መስፈርት የለውም፤ ለመንግሥቱ ስፋት ዐቅም ልክ የለውም፤ ለአገዛዙም ስፋት ወሰን የለውም ፤	5. The sea of his wisdom is unlimited, his merciful commands are countless, the range of his kingdom is immeasurable and his spacious government is boundless.
፮፤ ሥውር ውእቱ ዘኢይረክብ ብዎ በሕሊና ወምጡቅ ውእቱ ዘኢይጤይቅዎ በልቡና፤ ነዋኅ ውእቱ ዘኢይበጽሕዎ አንስርት ቀላይ ውእቱ ዘኢይፀብትዎ ዓሣት፤	፮፤ በሕሊና የማያገኙት ሥውር ነው፤ በልቡናም የማይረዱት ምጡቅ ነው፤ አንስርት የማይደርሱበት ረጅም ነው፤ ዓሣዎች የማይዋኙበት ጥልቅ ነው፤	6. So invisible is He that man can not find him by taking taught, so high is He that man can not understand him with his heart, so high is He that the eagles can not reach him, and so deep is He that the fish can not swim unto him.
፯፤ ልዑል ውእቱ እምአርእስተ አድባር፤ ወዕሙቅ ውእቱ እምዕመቀ ባሕር፤ ፅኑዕ ውእቱ ዘኢይትናስእዎ ነገሥት፤ መዋዒ ውእቱ ዘኢይትቃወምዎ መኳንንት፤	፯፤ ከተራሮች ራስ ይልቅ ከፍ ያለ ነው፤ ከባሕር ጥልቅ ነት ይልቅ ጥልቅ ነው፤ ነገሥታት የማይነሣሡበት ጽኑ ነው፤ መኳንንት የማይቃወሙት አሸናፊ ነው፤	7. He is higher than the heads of the mountains and deeper than the depth of the sea. He is so strong that the Kings can not rise against him, and He is so victorious that the rulers can not stand against him.
፰፤ ጠቢብ ውእቱ ዘያንዑል ምክረ ጠቢባን ማዕምር ውእቱ ዘያረስዕ ሕሊናተ መካርያን ኃያል ውእቱ ዘይፈትሕ ልጓማተ ጽኑዓን፤ ተባዕ ውእቱ ዘያደቅቅ አስናነ ኃጥአን ወይቀጠቅጥ መዝራዕተ ዕቡያን፤	፰፤ የጥበበኞችን ምክር የሚያጠፋ ጥበበኛ ነው፤ የሚመክሩትን ሰዎች አሳባቸውን የሚያስረሳ ዐዋቂ ነው፤ የጸኑ ልጓሞችን የሚፈታ ኃያል ነው፤ የኃጥአንን ጥርሶች የሚያደቅ፤ የትዕቢተኞችንም ክንድ የሚቀጠቅጥ ብርቱ ነው ፤	8. He is so wise that he can destroy the counsel of the wise, He is so omniscient that he can make the thought of the counsellers to be of none effect,[3] He is so mighty that he can loose the bridle of the strong, and He is so courageous that he can break into pieces the teeth of sinners and put down the arms of the haughty.

[3] Ps. 33:10.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፱፡ ክቡር ውእቱ ዘያንሥር ገጸ መደልዋን ከሀሊ ውእቱ ዘያአትት ብርሃነ ረሲዓን፡	፱፡ የግብዞችን ፊት የሚያዋ ርድ ክቡር ነው፣ የዝንጉ ዎችን ብርሃን የሚያርቅ ከሃሊ ነው፡	9. He is honourable that he can put to shame the face of the hypocrites, and He is so mighty that he can cast away the light of the filthy.
፲፡ ዋሕድ ውእቱ ዘእንበለ ቢጽ ወብሉት ውእቱ ዘእንበለ አዝማድ፣ ይትኃ ጐላ ሰማያት ወትማስን የብስ፣ ወኵሉ ይበሊ ከመ ልብስ ውእቱሰ ውእቱ ክመ እስከ ለዓለም፡	፲፡ ባልንጀራ የሌለው አንድ ነው፣ ዘመድ የሌለው የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ነው፡ ሰማያት ይጠፋሉ ፣ የብስም ትጠ ፋለች ፡ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃል ፣ እርሱ ግን እስከ ዘለዓለሙ እርሱ ነው ፡	10. He is the only one without equal, and He has absolute authority without the help of kinsmen. The heavens will be destroyed, and the land will vanish, and all will wax old like a garment, but he is the same for ever.[4]
፲፩፡ መንክር ውእቱ ተላህያ ለባሕር መንክርሰ እግዚአ ብሔር ውእቱ በአር ያሙ፣ አልቦ ዘይመስሎ ወአልቦ ዘይትዔረዮ እም ኵሉ ፍጥረት ወእም ኵሉሙ ደቂቀ አማልክት ባሕቲቱ አምላክ ወባሕቲቱ እግዚእ፣ ባሕቲቱ ፈጣሪ ወባሕቲቱ ገባሪ፡	፲፩፡ የባሕር መመላለስዋ ድንቅ ነው፣ ድንቅስ በልዕል ናው እግዚአብሔር ነው፣ የሚመስለው የለም፣ ከፍ ጥረትም ሁሉ ከአማልክ ትም ልጆች ሁሉ የሚ ተካከለው የለም፣ እርሱ ብቻ አምላክ ነው፣ እር ሱም ብቻ ጌታ ነው፣ ፈጣሪም እርሱ ብቻ ነው፣ ሠሪም እርሱ ብቻ ነው ፡	11. Wonderful is the movement of the sea, but more wonderful is God in his highest heaven. None resembles him and none competes with him from among all the creatures and all the children of gods. He himself alone is God; He himself alone is Lord; He himself alone is Creator and he himself alone is maker.
፲፪፡ ኢያንሥሥ መርድአ በእንተ ኪን ዘሐለየ ወኢይፈቅድ መምክረ በእንተ ምግባር ዘፈተወ፣ የአምር ኵሉ እምቅድመ ይኩን ከመ ዘኮነ ቅድመ ወዘኢተገብረ ከመ ዘተገብረ፡	፲፪፡ ስላሰበው ጥበብ ረዳት አይሻም፡ ስለ ወደደውም ሥራ መካር አይሻም፣ ሳይሆን ቀድሞ እንደ ሆነ አድርጎ፣ ያልተደረገ ውንም እንደ ተደረገ አድርጎ ሁሉን ያውቃል፡	12. He does not seek for a helper for the plan he conceived, and He does not want an adviser for the work he desired. He knows all things before they happen as if they had happened before and that which has not happened as if it had happened.
፲፫፡ የሐትት ሕሊና እንዘ ኢይሴአል ወይ ፈትን አልባበ እንዘ ኢየኀሥሥ ወይሬኢ ዘውስተ ጽል መት ዘእንበለ ማኀቶት፡	፲፫፡ ሳይጠይቅ ሕሊናን ይመረ ምራል፣ ሳይመረምር ልቡናን ይፈትናል፣ ያለ መብራት በጨለማ ያለ ውን ያያል ፡	13. He inspects the mind without asking, and examines the heart without seeking, and sees in darkness without light.
፲፬፡ ወየአምሮ ለጻድቅ እን በለ ይግበር ጽድቀ ወይ ቤይኖ ለኃጥእ እንበለ ይግበር ኃጢአተ ይሌብ ዎሙ ለልቡባን እንበለ ይፃኡ እምሐቋ አቡሆሙ፣ ወይጤይቆሙ ለኃጥአን እምከርሠ እሞሙ፡	፲፬፡ ጻድቁን ጽድቅን ሳይሠራ ያውቀዋል፣ ኃጥኡንም ኃጢአት ሳይሠራ ያው ቀዋል፣ ልበኞችን ከአባ ታቸው ወገብ (አብራክ) ሳይወጡ ያውቃቸዋል፣ ኃጥአንንም ከእናታቸው ማኅፀን ያውቃቸዋል ፡	14. He knows the righteous before they do righteousness, He perceives the sinners before they commit sin, He understands the prudent before they go out from the loins of their fathers and understands the sinners from the wombs of their mothers.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፲፭፤ አልቦ ዘይትኀብአ ወአ ልቦ ዘይሜወሮ ወአልቦ ዘይትከበት እምኔሁ ኵሉ ክሡት በኀቤሁ ወኵሉ ስጡሕ በቅድመ አዕይንቲሁ ኵሉ ጽሑፍ ውስተ መጽሐፉ ወኵሉ ጽውዕ በሕሊናሁ፤	፲፭፤ የሚሸሸገው የለም፣ የሚ ሠወረውም የለም፤ ከእር ሱም የሚሠወር የለም፣ ሁሉ በእርሱ ዘንድ የተገለጸ ነው፣ በዓይኖቹም ፊት ሁሉ የተዘረጋ ነው፣ ሁሉ በመጽሐፉ የተጻፈ ነው፣ በሕሊናውም ሁሉ የተጠራ ነው፤	15. Nothing is hidden, nothing is concealed and nothing is invisible unto him, but all is open unto him and all is spread before his eyes and all is written in his book and all is called to his mind.
፲፮፤ ይገብር ዐቢያተ ዘአልቦ ኑልቍ ክቡራተ ወመን ክራተ ዘአልቦ ዐሠር፣ ዕፁብ ግብሩ እምዘርኢነ፤ ወመ ንክር ኃይሉ እምዘሰማዕነ ወመድምም ስብሐቲሁ እምዘነገሩነ ፤	፲፮፤ ቁጥር የሌላቸው ታላላቆ ችን፣ መመርመር የሌለ ባቸውን የተደነቁ የከበሩ ሥራዎችን ይሠራል ፣ ሥራው ከአየነው ይልቅ ዕፁብ ነው፣ ኃይሉም ከሰማነው ይልቅ ድንቅ ነው፣ ጌትነቱም ከነገሩን ይልቅ ድንቅ ነው ፤	16. He does the great, countless, honourable and marvellous deeds which are unsearchable. His works are more wonderful than we can comprehend; his power is more marvellous than anything we have heard and his glory is more astonishing than any had told us.
፲፯፤ ውእቱ ገብረ ብርሃነ እም ጽልመት ወየአምር ፈሊ ጦቶ ለደመና ይከፍሎ ለማይ ዘከመ ፈቀደ ወይ ሜውር ኅሩያነ በደመና፡፡	፲፯፤ ከጨለማ ለይቶ ብርሃንን ፈጠረ፤ ደመናውን መለ የት ያውቃል፣ ውኃውን እንደ ወደደ ይከፍለዋል፤ የተመረጡትን በደመና ይሠውራል ፡፡	17. He made light out of darkness, he knows how to divide clouds, He divedes water at his pleasure and He hides the elect with clouds.
✱ ✱ ✱	✱ ✱ ✱	✱ ✱ ✱
፲፰፤ ሣረራ ለምድር ወሠርዐ አምጣኒሃ ወተከለ ከመ ወኢምንት ሕላቃቲሃ ወአስተኀደረ መዓዝኒሃ፤	፲፰፤ ምድርን ፈጠራት፤ መጠ ንዋንም አዘጋጀ፣ ፍጻሜዋ ንም እንደምንም ተከለ፣ ማዕዘንዋንም አጸና፤	18. He built the earth and prepared its boundaries, and established its ends in the way he saw, and strengthened its corners.
፲፱፤ ሐፀራ ለባሕር በአናቅጽ አመ ' ወፅአት እምከርሠ እማ፤ ወረሰየ ላቲ ደመና ልብሳ፣ ወበጊሜ ጠብለላ፣ ወገብ ረላቲ ወሰነ ውሜመ ውስቴታ መዓፁተ ወመና ሥግተ፣ ወይቤላ እስከ ዝየ ብጽሒ ወኢትትዐደዊ እምወሰንኪ፤ ዳዕሙ ይት ከወስ ማዕበልኪ በውስቴ ትኪ፤	፲፱፤ ባሕርን ከእናትዋ ሆድ በወጣች ጊዜ በበሮች አጠራት፣ ልብሷንም ደመና አደረገ ላት፣ በጉም ጠቀለላት፣ ወሰንም አደረገላት ፣ በውስጥዋም መዝጊያዎ ችንና ቍልፎችን አደረገ ላት፣ እስከዚህ ድረሺ፣ ከወሰንሽም አትተላለፊ፣ ማዕበልሽ በውስጥሽ ይመ ላለስ (ይነቃነቅ) እንጂ አላት፤	19. He fenced the sea with doors when it went out of it mother's womb,[5] He made the clouds to be its clothes, and wrapped it with mist, He limited it and put into it doors and locks and said to it, "Reach here and do not go beyond your limit, but your storm will move in you."

[5] When it was created.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፳፡ ወበላዕሌሃ ተሠርዐ ጎሐ ጽባሕ፣ ወኮከበ ጽባሕኒ አእመረ ትእዛዘ ውእቱ ነሥአ ፅቡረ እምድር ወፈጠረ ዘሕያው ወረ ሰዮ ይትናገር ዲበ ምድር፡	፳፡ በበላይዋ ላይ የንጋት ብር ሃን ተዘጋጀ፡ የአጥቢያ ኮከብም ትእዛዙን ዐወቀ፣ እርሱ ከምድር ጭቃን ነሥቶ ሕያው የሆነውን ፈጠረ፣ በምድርም ላይ እንዲነጋገር አደረገው፡	20. There was arranged over it the light of dawn, and the morning star knew his commandment. He took mud from the earth and created the living being and made him speak on the earth.
፳፩፡ ውእቱ በጽሐ እስከ አጽ ናፈ ባሕር ወአንሶሰወ ውስተ ዐሠረ ቀላይ፡	፳፩፡ እርሱ እስከ ዓለም ዳርቻ ደረሰ ፡ በጥልቅ ፍለጋም ተመላለሰ ፡	21. He reached the ends of the sea and walked in the paths of the deep.
፳፪፡ ሎቱ ይትረኃዉ አናቅጸ ሞት እምግርማሁ ወአ ጸውተ ሲኦል ይደነግፁ እምከመ ርእይዎ ውእቱ የአምር ራኃበ ዘታሕተ ሰማይ ወዘይከውን በመ ልዕልተ ሰማይ፡	፳፪፡ ከግርማው የተነሣ የሞት ደጆች ይከፈታሉ፣ የሲኦል በሮችም ባዩት ጊዜ ይደ ነግጣሉ፣ ከሰማይ በታች ያለውን ስፋቱን፡ ከሰማይ በላይ የሚሆነውንም እርሱ ያውቃል ፡	22. To him the doors of death will be opened because of his glory, and the doorkeepers of hell will be afraid as soon as they see him. He knows the spaciousness under heaven and that which happens above heaven.
፳፫፡ ወበትእዛዙ ይወፅእ ሐመዳ እመዝገቡ ወይት መየጥ አዜብ ዘታሕተ ሰማይ፣ ያጸንዖ ለዝናም በፍናተ በድው ከመ ይዝንም ብሔረ ኃበ አልቦ ሰብእ ወኢይነብሮ ፅጎለ እመሕያው፡	፳፫፡ በርሱ ትእዛዝ ዋግ ከመ ዝገቡ ይወጣል፣ ከሰማይ በታች ያለ አዜብ (ነፋስ) ይመላለሳል፣ ዝናምን በምድረ በዳ ያጸናዋል፡ ሰው በሌለበትና የሰው ልጅ በማይኖርበት ይዘ ንም ዘንድ ፡	23. Through his commandment frost comes out of its treasure and the wind blows under heaven. He leads the rain along the way of the wilderness to fall on the country where there is no man and wherein mortal man does not live.
፳፬፡ ውእቱ ዐቀመ ሙሐዘ ማይ ወያርኅ ክረምተ በበ ዓመት ወያመጽኦ ለሐጋይ ድኅረ በዕድሜሁ፣ ውእቱ ይጼውዖ ለደመና በቃሉ ወያወሥኦ ማይ እንዘ ይርዕድ፡	፳፬፡ እርሱ የውኃውን መፍ ሰሻ ወሰነ ፣ ክረምትንም በያመቱ ይከፍታል፣ በጋውንም ኋላ በጊዜው ጊዜ ያመጣዋል፣ ደመና ውንም በቃሉ ይጠራ ዋል፣ ውኃም እየተንቀ ጠቀጠ ይመልስለታል፡	24. He established the course of water and opens the winter every year and brings the summer back in its due time. He calls the clouds with his word and water answers him trembling.
፳፭፡ ውእቱ ይፈንዎ ለፀዓዕ ወየሐውር ወይሠጠዎ እዝ ይብል ምንት ውእቱ፣ ውእቱ ይኄልቆ ለደመና በጥበቡ ወያጸንዖ ለሰማይ ዲበ ምድር፡	፳፭፡ ብልጭልጭታውን እርሱ ይልከዋል ፣ እርሱም ይሄዳል፣ ምንድር ነው እያለ ይመልስለታል፣ እርሱ ደመናን በጥበቡ ይቈጥረዋል ፣ ሰማይን (ጠፈርን) ወደ ምድር ያዘነብለዋል፡	25. He sends the thunderbolt and it goes and answers him saying: What shall I do? He counts the clouds through his wisdom and hangs the heaven over the earth.
፳፮፡ ውእቱ ባሕቲቱ ለብሰ ኃይለ እምአርያም ወተ ረሰየ በስብሐት ወበ ክብር፡	፳፮፡ እርሱ ብቻ የአርያምን ኃይል ለበሰ፣ በምስጋናና በክብር ተጌጠ ፡	26. He alone puts on the power of the highest heaven and is adorned with glory and honour.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፳፯፡ ዘኪያሁ ይቄድሱ ኪሩ ቤል እሳታውያን ወሱራ ፊል ልቡሳነ ብርሃን በቃል ዘኢየዐርፍ ወበ አፍ ዘኢያረምም ወበ ልሳን ዘኢይደክም፡ ወይ ብሉ ኵሎሙ ኀቢሮሙ በፅዱ ቃለ አውሥኦ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግ ዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ፡	፳፯፡ እሳታውያን ኪሩቤል ብርሃን የለበሱ ሱራፌ ልም እርሱን ያመሰግ ናሉ፡ በማያርፍ ቃል ዝም በማይል አፍ፡ በማይደክምም አንደበት ሁሉም ተባብረው ተሰ ጥዎ ባለበት ባንድ ቃል፡ የጌትነትህ ምስ ጋና በሰማይ በምድር የመላ ፍጹም አሸናፊ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ እግዚአብሔር ይላሉ ፡	27. Him hallow the fiery Cherubim and the Seraphim dressed in light with ceaseless words and a mouth which does not keep silent and a tongue which does not tire; and all say together with one voice answering: Holy holy holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the holiness of your glory.
፳፰፡ ይ. ዲ. አውሥኦ!	፳፰፡ ይ.ዲ. ተሰጥዎን መልሱ!	28. *Deacon*: You answer.
፳፱፡ ይ. ሕ. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባ ዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድ ሳተ ስብሐቲከ፡	፳፱፡ ይሕ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብ ሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው፡	29. *People*: Holy holy holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the holiness of your glory.
፴፡ ይ. ካ. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ እግዚአብ ሔር እግዚኦሙ ለቅዱ ሳን ወመልዐ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐ ቲከ፡	፴፡ ይ.ካ. የቅዱሳን ጌታ እግዚአብሔር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነህ የጌት ነትህም ምስጋና በሰማይ በምድር መላ፡	30. *Priest*: Holy holy holy are you God, Lord of the holy ones, the holiness of your glory fills heaven and earth.
፴፩፡ ኵሉ እምኔሁ፡ ወኵሉ በእንቲአሁ፡ ወኵሉ ዘዚ አሁ፡ ሰማይ ሎቱ ፡ ወሰማየ ሰማያት እንቲ አሁ ፡ ራኀበ አርያም መንበረ ክብሩ፡ ወስፍሐ ምድር መከየደ እገሪሁ፡	፴፩፡ ሁሉ ከርሱ ነው፡ ሁሉም ስለ እርሱ ነው፡ ሁሉም የርሱ ነው፡ ሰማይ በርሱ ነው፡ ከሰማያት በላይ ያለ ሰማይም የርሱ ነው፡ የአርያም ስፋት የክብሩ ዙፋን ነው፡ የምድርም ስፋት የእግሩ መመላለሻ ናት፡	31. All is from him, all is for his sake, and all is his. Heaven is his, and the heaven of heavens is his. The breadth of the highest heaven is the throne of his glory, and the wide earth is his footstool.
፴፪፡ ፀሐይ ዚአሁ ወወርኀ ሎቱ፡ ወከዋክብት ተግ ባረ እደዊሁ ፡ ደመናት ሐዋርያቲሁ፡ ወነፋሳት ሠረገላቲሁ፡ ወእሳት ዐረፍተ ቤቱ፡	፴፪፡ ፀሐይ የርሱ ነው፡ ጨረ ቃም ከርሱ ነው፡ ከዋክ ብትም የእጁ ሥራ ናቸው፡ ደመናት መልክ ተኞቹ፡ ነፋሳትም ሠረገላ ዎቹ ናቸው፡ እሳትም የቤቱ ግርግዳ ነው፡	32. The sun is his, the moon is his, and the stars are the work of his hands. Clouds are his messengers, winds are his chariots and fire is the wall of his house.
፴፫፡ ማይ ጠፈረ ቤቱ ፡ ሰሌዳ በረድ ጸፍጸፈ ዐውዱ፡ ወብርሃናት ደባ ትሪሁ፡ ወመብረቀ ስብ ሐት መንጦላዕተ ምሥ ዋራቲሁ፡ ወውስተ አየ ራት ነሶላዉ ፡	፴፫፡ የቤቱ ጠፈር ውኃ ነው፡ የዙሪያውም ጸፍጸፍ የበረድ ሰሌዳ ነው፡ ድን ኳኖቹ ብርሃናት ናቸው፡ የመሠወሪያ መጋረጃውም የብርሃን መብረቅ ነው፡ መመላለሻውም በአየር ነው ፡	33. Water is the roof of his house, the gables of it are snow, light is his tabernacle, the lightning of glory is the veil of his hiding-place, and his going is in the air.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፴፬፤ ዘበፀዐዕ ድምፀ ንባቡ፣ ወቃለ ነጐድጓዱ በሠረገ ላት፣ ባሕር ዓመቱ፣ ወሐይዝተ አፍላግ ቅኑ ያቲሁ፣ ቍር ወአስሐ ትያ ገባርያነ ሥምረቱ ፤	፴፬፤ የመናገሩ ድምፅ በብ ልጭልጭታ ያለ ነው፣ የነጐድጓዱ ቃል በሠረ ገላዎች አለ፣ ባሕር ባሪያው ናት፣ የወንዝ ፈሳሾች ተገዥዎቹ ናቸው ፣ ቍር አስሐት ያም ፈቃዱን የሚሠሩ ናቸው ፤	34. The voice of his speech is in the thunderbolt, the sound of thunder is in the chariots, the sea is his hand-maid, the water-flood of the rivers is his servant, and cold and frost do his pleasure.
፴፭፤ የዐርግ ደመናተ እም አጽናፈ ምድር ፣ ወገ ብረ መብረቀ ለጊዜ ዝናም፣ ወይክው ዝና ማተ ከመ ነጠብጣበ ማሕየብ፣ ይዘርዎ ለጊሜ ከመ ሐመድ፣ ወያ ወርድ በረደ ከመ ፍተ ታት ወያሕመለምል ሣዕረ ለእንስሳ፤	፴፭፤ ከምድር ዳርቻ ደመና ውን ያወጣል ፣ መብረ ቅንም በዝናም ጊዜ አደረገ፣ ዝናምንም እንደ መሸረብ ነጠብጣብ ያፈሳል፣ ጉምን እንደ አመድ ይበትነዋል፣ በረ ድንም እያጠቃቀነ ያወ ርዳል፤ ለእንስሳም ሣሩን ያለመልማል ፤	35. He causes the clouds to ascend from the ends of the earth, He makes lightning for the rain,[6] He pours rain like drops from a strainer, He scatteres the hoa-rfrost like ashes, He casts forth his ice like morsels,[7] and He causes the grass to grow for the cattle.[8]
፴፮፤ ይገብር በከመ ሐለየ፣ ወይፈጽም በከመ ወጠነ ወያጠዐጥዕ በከመ ፈቀደ፣ ያሐስም ወያሜኒ፣ ያነዲ ወያብዕል፣ ያንሥር ወያ ከብር፣ ይቀትል ወያ ሐዩ፣ ያደዊ ወይፈውስ ይኴንን ወያጸድቅ ፤	፴፮፤ እንዳሰበ ያደርጋል፣ እንደ ጀመረም የጀመረውን ይፈጽማል፣ እንደ ወደ ደም ያከናውናል ፣ ያሳ ዝናል፣ ደስ ያሰኛል፣ ያደኸያል፣ ባለጸጋም ያደ ርጋል፣ ያዋርዳል፣ ያከ ብራልም፣ ይገድላል ያድ ናልም፣ ድውይ ያደር ጋል፣ ይፈውሳልም፣ ይኮ ንናል፣ያጸድቃልም፤	36. He does according to his thought, complets what he began, orders according to his will. He makes sad and gives pleasure, impoverishes and enrichs, dishonours and honours, kills and quickens, makes sick and heals, judges and justifies.
፴፯፤ ለዘፈቀደ ይምሕር ወለ ዘፈቀደ ያዐፅብ ወለዘሂ መሐረ ይምሕሮ ወለ ዘሂ ተሣሃለ ይሣሃሎ፤	፴፯፤ የወደደውን ይምራል፣ ሊያስጨንቀው የወደደ ውን ያስጨንቃል፣ የሚ ምረውን ይምረዋል ፣ ይቅር የሚለውን ይቅር ይለዋል ፤	37. He spares to whom he wills to spare, he distresses to whom he wills to distress, He will have mercy on whom he will have mercy, will have compassion on whom He will have compassion.
፴፰፤ ይ. ሕ. በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ፤	፴፰፤ ይ.ሕ. አምላካችን ሆይ፣ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይደለም ፤	38. *People*: According to your mercy, our God, and not according to our sins.
፴፱፤ ይ. ካ. ኄር ዘእንበለ እከይ፣ ወየዋሕ ዘእንበለ በቀል ወዕጉሥ ዘእንበለ መዓት፣ ጻድቅ ዘእንበለ ኃጢአት፤ ወንጹሕ ዘእ ንበለ ርስሐት ወራትዕ ዘእንበለ ጥውየት፤	፴፱፤ ይ.ካ. ክፋት የሌለበት ቸር፣ በቀል የሌለበት የዋህ፣ ቍጣ የሌለበት ትዕግሥተኛ፤ ኃጢአት የሌለበት ጻድቅ፤ እድፍ የሌለበት ንጹሕ ፣ ጠማ ምነት የሌለበት ቅን ነው፤	39. *Priest*: He is kind without evil, meek without revenge, patient without wrath, r i g h t e o u s without sin, pure without filthiness, and upright without perversion.

[6] Ps. 135:7.
[7] Ps. 147:16,17.
[8] Ps. 104:14

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፵፡ ወሀቢ ዘእንበለ ክልአት ወጸጋዊ ዘእንበለ ደን ፅዎ ሠራዬ ኃጢአት ዘእንበለ ቂም ወቅንዓት፡	፵፡ ያለመከልከል ሰጪ፣ ያለ መንፈግ ለጋስ፣ ያለ ቂምና ያለቅናት ኃጢአ ትን የሚያስተሠርይ ነው፡	40. He is the giver without hindrance, gracious without stint, the forgiver of sin without revenge or envy.
፵፩፡ ቅሩብ ውእቱ ለእለ ይጼ ውዕዎ ወገባሬ ሠናያት ለእለ ይፈርህዎ፣ አን ቀጽ ርኅው ለእለ ይጐ ደጉድዎ ፍኖት መጽያ ሕት ዘእንበለ ማዕቅፍ፡ ወዐሠር ንጹሕ ዘእንበለ አሥዋክ ፡	፵፩፡ ለሚጠሩት ሰዎች የቀረበ ነው፣ ለሚፈሩትም በጎ ውን ነገር የሚያደርግ ነው፣ ለሚያንኳኩ ሰዎች የተከፈተ በር ነው፣ ያለ መሰናክል ጥርጊያ ጎዳና፣ እሾህ የሌለበት ንጹሕ ፍለጋ ነው ፡	41. He is near unto those who call upon him,[9] doer of good unto those who fear him, He is the open door unto those who knock at him, the prepared way without a stumbling-block and the pure path without thrones.
፵፪፡ ውእቱ ባሕቲቱ እግዚአ ብሔር አምላከ አማል ክት ወእግዚአ አጋዕዝት፡	፵፪፡ የአማልክት አምላክ፣ የአጋዕዝት ጌታ እግዚ አብሔር እርሱ ብቻ ነው ፡	42. He alone is God, the God of gods and Lord of lords.
፵፫፡ ወእምዝ ሶበ ርእየ ከመ አበቍዐ ለአድኅኖተ ዓለም ደመ ነቢያት ቅዱሳን እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ፣ ፈነወ ለነ ወልዶ መድኀኒ (ወመቤዝወ) ከመ ይባ ልሕ ወይቤዙ ወያብእ ቅድሜሁ ተዝካረ ሕያ ዋን ወሙታን፡	፵፫፡ ከዚህ በኋላ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እንዳ ልጠቀመ ባየ ጊዜ ቤዛ መድኃኒት የሚሆን ልጁን ሰደደልን፣ ፈጽሞ ያድን ዘንድ በፊቱ የሕያዋን ንና የሙታንን መታሰቢ ያም ያገባ ዘንድ ፡	43. After this, when he saw that the blood of the holy prophets, from the blood of the righteous Abel unto the blood of Zacharias Son of Barachias, was not sufficient for the salvation of the world, He sent unto us his Son, a Saviour and Redeemer, to save us and redeem us and take before him the remembrance of the living and the dead.
፵፬፡ ይ. ዲ. በእንተ ብፁዕ ፡	፵፬፡ ይ.ዲ. በእንተ ብፁዕ፣ (ቅዳ. ሐዋ. ከቍ. ፮-፱)፡	44. *Deacon*: For the sake of the blessed ... (*Anaphora of the Apostles* No. 6-9)
፵፭፡ ይ. ካ. ንፍቅ ጸሎተ ቡራኬ፡	፵፭፡ ይካ. ንፍቅ ጸሎተ ቡራኬ፣ (ቅዳ. ሐዋ. ከቍ፲-፳፩)	45. *The assis-tant priest shall say the Prayer of Benediction. (Anaphora of the Apostles No.* 10-21)
፵፮፡ ይ. ዲ. ንፍቅ መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሉሙ ሕዝበ ክርስቲያን ፡	፵፮፡ ይ.ዲ. ንፍቅ፣ አቤቱ የጳጳ ሳቱን አለቆች፣ ጳጳሳቱ ንና ኤጲስቆጶሳቱን፣ ቀሳ ውስቱንና ዲያቆናቱን፣ የክርስቲያንንም ወገኖች ሁሉ ማራቸው፣ ይቅርም በላቸው ፡	46. *Asst Deacon*: Lord, pity and have mercy upon the patriarchs, archbishops, bishops, priests, deacons and all the Christian people.
፵፯፡ ይ. ካ. መጽአ እንዘ ህልው በህየ ወተፈነወ እንዘ ኢይደምፅ በዝየ ፡	፵፯፡ ይካ. በወዲያ ሳለ መጣ፣ በወዲህም ሳይሰማ ተላከ፡	47. *Priest*: While He was yet there He came and He was sent without it being noised abroad.

[9] Ps. 145:18.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
፵፰፡ ይ. ዲ. እለ ትነብሩ ተንሥኡ ፡	፵፰፡ ይ.ዲ. የተቀመጣችሁ ተነሡ፡	48. *Deacon*: You, that are sitting, stand up.
፵፱፡ ይ. ካ. ወረደ እንዘ ኢይትሐወስ እመንበሩ ወኢያንቀለቅል እመካኑ፡	፵፱፡ ይ.ካ. ከዙፋኑ ሳይነቃነቅ፡ ከቦታውም ሳይናወጥ ወረደ፡	49. *Priest*: He came down without being moved from his throne and without being removed from his place.
፶፡ ይ. ዲ. ውስተ ጽባሕ ነጽሩ ፡	፶፡ ይ.ዲ ወደ ምሥራቅ ተመ ልከቱ ፡	50. *Deacon*: Look to the east.
፶፩፡ ይ. ካ. ተፀንሰ በከርሥ እንዘ ምሉዕ በኵለሄ ወተወልደ እንዘ ኢያርኅ ማኅተመ ድንግልናሃ ፡	፶፩፡ ይ.ካ. በሁሉ ምሉዕ ሲሆን በማኅፀን ተፀነሰ፣ ማኅተመ ድንግልናን ሳይ ከፍት ተወለደ ፡	51. *Priest*: He was conceived in the womb while he was filling everywhere, was born without opening the seal of virginity.
፶፪፡ ይ. ዲ. ንነጽር ፡	፶፪፡ ይ.ዲ. እናስተውል ፡	52. *Deacon*: Let us give heed.
፶፫፡ ይ. ካ. ተሐፅነ ከመ ሕፃን ወልሕቀ በበሕቅ እስከ ወርዘወ በአምጣነ ብእሲ፡	፶፫፡ ይ.ካ. እንደ ሕፃን አደገ፡ በሰው መጠን እስኪጐለ ምስ ድረስ በዮጥቂቱ አደገ፡	53. *Priest*: He grew like an infant, and grew little by little until he matur-ed like a man.
፶፬፡ በ፴ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ከመ ያንጽሐነ እምኃጢአት በሕፅበተ ዳግም ልደት፡	፶፬፡ በሠላሳ ዘመን በዮርዳኖስ ተጠመቀ፣ በሁለተኛ ልደት መታጠብ ከኃጢ አት ያነጻን ዘንድ ፡	54. At the age of thirty He was baptized in Jordan to purify us from sin by the washing of regeneration.
፶፭፡ እምኀበ ዲያብሎስ ተመ ከረ፣ ርኀበ ወጸምዓ፣ አንሶሰወ ወአስተርአየ እንዘ ይሰብክ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት ፡፡	፶፭፡ ከዲያብሎስ ዘንድ ተፈተነ፣ ተራበ፣ ተጠማም ፡ የሰ ማይ መንግሥት ወንጌ ልን እያስተማረ ታይቶ ተመላለሰ፡፡	55. He was tempted by the devil, He hungered and thirsted, walked and appeared preaching the gospel of the kingdom of heaven.
✱ ✱ ✱	✱ ✱ ✱	✱ ✱ ✱
፶፮፡ በዝየ ዕርገተ ዕጣን ፣ ይ. ሕ. ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ፡	፶፮፡ በዚህ ጊዜ ቁሱ ዕጣኑን ያሳርግ ፣ ይ.ሕ. አቤቱ በመንግሥትህ አስበን፣ (ቅዳ. ሐዋ.ቍ. ፴፬)	56. *At his time he shall offer incense.* *People*: Remember us, Lord, in your kingdom ... (*Anaphora of the Apostle No.* 34)
፶፯፡ ይ. ካ. ወእምዝ ሰፍሐ እደዊሁ ዲበ ዕፀ መስ ቀል ለሕማም ከመ ይፈ ውስ ቍስለ ሕሙማን በንዝኃተ ደሙ ፡	፶፯፡ ይ.ካ. ከዚህ በኋላ ለሕ ማም በዕፀ መስቀል ላይ እጁን ዘረጋ፣ በደሙ መረጨት የሕሙማንን ቍስል ያድን ዘንድ ፡	57. *Priest*: Then he stretch-ed forth his hands on the tree of the cross for suffering to cure the wound of the sick by the sprinkling of his blood.

ግዕዝ	አማርኛ	ENGLISH
ግዕዝ	አማርኛ
ሊጦን ዘቀዳሚት ይ. ካ. ቀዳሜ ጸጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይሉ ወጥበቡ ለአቡሁ፣ እስመ አንተ ውእቱ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘያአትት ኃጢአተ ዓለም ተሣሃለነ እስመ ወረድከ እምሰማይ በመስፈርተ ጥበቡ ለአቡከ ከመ ታድኅን ልሕኵተከ ዘአንተ ለሐኮ መዋቴ ዘይማስን፣ ዘየሐውር በክነፈ ነፋስ ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ፣ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት ዘይኔጽራ ለምድር ወይሬስያ ከመ ትርዐድ፤ ዘይገሥሦሙ ለአድባር ወይጠይሱ፣ በመንፈሰ ጸጋከ አጽንዖሙ ለሕዝብከ፣ አንተ አኃዜ ዓለም እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣ ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ በመንፈሰ ጸጋከ አስተፍሥሖሙ ለሕዝብከ፣ እስመ አንተ ውእቱ መቅለሌ ዕፁብ ረዳኤ ምንዱብ፣ ሠርኃሙ ለሐዋርያት ንዋዮሙ ለነዳያን፣ ተስፋሆሙ ለቅቡዓን መንሥኤሆሙ ለሙታን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይሉ ወጥበቡ ለአቡሁ፣ ኪያከ ነአኵት ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ ይ. ሕ. አሜን፡፡ *** ሊጦን ዘእሑድ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለአምላከ ምሕረት ዘረዳእኮ ለአብርሃም አመ ይቀት ሎሙ ለነገሥት ዘአድኅንኮ ለይስሐቅ እምነ መጥባሕት ዘመራሕኮ ለያዕቆብ በውስተ መንገድ ወአስተርአይኮ በራእየ ሌሊት በኀበ አቀሞን ለሐውልት ዘአዕበይኮ ለዮሴፍ በብሔረ ባዕድ እግዚአብሔር አምላክነ፣	የቀዳሚት ሊጦን ፣ ይ.ካ. የስጦታ መጀመሪያ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቱ ኃይሉ ጥበቡ ነው፣ የዓለምን ኃጢአት የምታርቅ የእግዚአብሔር በግ አንተ ነህና፣ ይቅር በለን ፣ በአባትህ በጥበቡ መስፈርት ከሰማይ ወርደሃልና፣ አንተ የፈጠርከውን ሟች ተለዋጭ የሆነ ፍጥረትህን ታድን ዘንድ፣ በነፋስ ክንፍ የሚሄዱ መላእክትን ረቂቃን፣ የሚያገለግሉትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው፣ ምድርን አይቶ እንድትንቀጠቀጥ ያደርጋታል፣ ተራራዎችንም ይዳስሳቸዋል፣ ይጨሳሉ፣ ዓለምን የያዝህ አንተ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፣ በስጦታህ መንፈስ ወገኖችህን አጽናቸው፣ ይ.ዲ. ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፤ ይ.ካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን ሆይ፣ በስጦታህ መንፈስ ወገኖችህን ደስ አሰኛቸው፣ ጭንቁን ነገር የምታቀል፣ የተቸገረውን የምትረዳ አንተ ነህ፣ የሐዋርያት ጌጣቸው፣ የነዳያን ገንዘባቸው፣ ተስፋ ላጡ ሰዎች ተስፋቸው፣ ሙታንንም የምታነሣቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፣ ለአብ ኃይሉ ጥበቡ የምትሆን አንተን እናመሰግናለን፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡ *** የሠርክ ሊጦን፣ ይ.ካ. የምሕረት አምላክን ዳግመኛ እንማልደዋለን፣ ነገሥታቱን በወጋቸው ጊዜ አብርሃምን ያዳንከው፣ ይስሐቅን ከመጥባሕት (ከመሠዋት) ያዳንከው፣ ያዕቆብን በመንገድ የመራኸው ፣ ድንጋዩን ባቆመበት ቦታ ሌሊት በራእይ የታየኸው፣ ዮሴፍን በባዕድ ሀገር ከፍ ከፍ ያደረግኸው አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ጸልዩ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣ ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ ዘኀደፍከ ለኖኅ በውስተ ታቦት፤ ወለዳንኤል እምአፈ አናብስት ወለሶስና እምእደ ረበናት፣ ዘለአኮ ለሙሴ ምስለ ዐቢይ ረድኤት ዘመራሕከሙ ለሕዝብከ መዓልተ በደመና ወኵሉ ሌሊተ በብርሃነ እሳት፣ ዘተናገርከ በዲበ ነቢያት፣ ወአስተርአይከ ጸጋከ ላዕለ ሐዋርያት እንዘ ጉቡኣን እሙንቱ ውስተ ፎዱ ቤት ወረደ ላዕሌሆሙ መንፈስ ቅዱስ ከመ ዘእሳት ወተናገሩ በነገረ ኵሉ በሐውርት፣ ውእተ መንፈስከ ፈኑ ዐማዴ ሰማይ ወምድር ባርክ ማኅበረነ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት፣ በፎዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጊዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ ይ. ሕ. አሜን፡፡ * * * ሊጦን ዘሠርክ፣ ይ. ካ. አምላክነ ዘዲበ ኪሩቤል ትነብር እምኀበ መላእክት ትትአኰት ወትሴባሕ፣ አንተ ውእቱ ዘከፈልከነ ንባእ ውስተ ጽርሐ ቅዱስ ማኅደርከ ንዘከር ቅድሳተ ስብሐቲከ ወንፍዲ ለከ ዘሠርክ አኰቴተ፣ አንተ ተወከፍ ዘኵልነ ስክየተ ወበቍዔተ በተአምኖ በውስተ ልብው ዘበሰማያት ምሥጢርከ በዜና ሠናይ መዓዛ ፣ ዕቀብ ኵሉነ ዘእንበለ ፃሕብ ወዘእንበለ ተመውዖ ወዘእንበለ ማዕቅፍ፣ አድኅን አእጋረነ እምዳኅፅ ወአዕይንተነ እምአንብዕ ወነፍስተነ እሞተ ኃጢአት፣ ወደምረነ ምስለ እለ ድኅኑ ብከ በጸሎተ ኵሎሙ እለ እምዓለም አሥመሩከ ፣	ይ.ዲ. ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. እውነት ነው፣ አቤቱ አምላካችን ኖኅን በመርከብ ያሻገርከው አንተ ነህ፣ ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ ያዳንከው፣ ሶስናን ከረበናት እጅ ያዳንካት፣ ሙሴን ከታላቅ ረድኤት ጋራ የላክኸው፣ ወገኖችህንም ቀን በደመና፤ ሌሊቱን ሁሉ በእሳት ብርሃን የመራኻቸው፣ በነቢያት የተናገርህ፣ በሐዋርያት ላይ ጸጋህን የገለጽህ አንተ ነህ፣ በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ሆኖ በላያቸው ወረደ፣ በሀገሩ ሁሉ ቋንቋ ተናገሩ፣ ሰማይንና ምድርን የፈጠርህ አንተ ይህንን መንፈስህን ላክልን፣ በየጊዜው በየሰዓቱ ሁሉ አንድነታችንን ባርክልን ፣ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡ * * * የሠርክ ሊጦን ፤ ይ.ካ. በኪሩቤል አድረህ የምትኖር አምላካችን ሆይ በመላእክት ዘንድ ትከበራለህ ትመሰገናለህ ፣ የተቀደሰ ማደሪያህ ከሆነ አዳራሽ እንገባ ዘንድ ያደልከን አንተ ነህ ፣ የምስጋናህን ቅድስና እናስብ ዘንድ ፣ የማታውንም ምስጋና እናቀርብልህ ዘንድ የሁላችንን መማፀን ተቀበል ፣ ሰማያዊ ምሥጢርህን በምናስብበት እምነት ረብህ ጥቅምን ስጠን፣ ሁላችንንም ያለመጨነቅ ያለ መሸነፍ ያለ መሰናከል ጠብቀን፣ እግሮቻችንን ከድጥ፣ ዓይኖቻችንን ከዕንባ፣ ሰውነታችንን ከኃጢአት ሞት አድነን፣ ከቀድሞ ጀምሮ ያገለገሉህን የወዳጆችህን ሁሉ ልመና አስበህ በአንተ ከዳኑት ጋራ ቍጠረን ፣

ግዕዝ

በፈዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጎዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፣

ይ. ሕ. አሜን ፡፡

* * *

ዓዲ ሊጦን ዘሠርክ፣

ይ. ካ. ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእጎዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እስመ ረሰየነ ተድላ ካዕበ ውስተ ዝንቱ መካን ቅዱስ ንቁም ንሰብሕ ወንዘምር ለዘበኵሉ ቅዱስ ወብፁዕ ስመ ዚአሁ፣ ዘኵሎ ይእጎዝ እግዚብሔር አምላክነ፣

ይ. ዲ. ጸልዩ፣

ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣

ይ. ካ. እግዚኦ ዘኵሎ ትእጎዝ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ በከመ ዐቀብከነ ኑኃ ሌሊት ወአብጻሕከነ ካዕበ ውስተ ብርሃነ ሠርክ ዕቀበነ በኑኃ ሌሊት፣

ሱላሜ ዘእንበለ ኃጢአት ሠርከ ወሌሊተ ጸግወነ፣ ወአድኅነነ እምፍርሃተ ሌሊት ወእምትካዝ ዘይወስድ ውስተ ጽልመት፣ እምሰብእ ዐማፂ ወሀባሊ ባልሐነ፣ ዘአበስነ ወዘተሠወረነ ሕገ ሰብእ አናኅሲ ለነ፣ እስመ ኄር ወመፍቀሬ ሰብእ አንተ እግዚአብሔር አምላክነ፣

በፈዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጎዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤

ይ. ሕ. አሜን፡፡

* * *

አማርኛ

በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ አሜን፤

ይ.ሕ. አሜን ፡፡

* * *

ዳግመኛ የሠርክ ሊጦን ፣

ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ፣ ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር በሁሉ ለተመሰገነና ለተደነቀ ስሙ እንዘምር እና መሰግን ዘንድ፣ በተመሰገነው በዚህ ቦታ እንድንቆም ዳግመኛ ደስታን ሰጥቶናልና ፣ ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ነው፣

ይ.ዲ. ጸልዩ ፣

ት.እ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣

ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ ጌታ ሆይ ፣ እንለምንሃለን ፣ እንማልድሃለን፣ በሞላው ሌሊት እንደጠበቅኸን ወደቀኑም ብርሃን ዳግመኛ እንዳደረስከን በሚመጣው ሌሊት ጠብቀን፣

ፍቅርን ያለ ኃጢአት በሠርክና በሌሊት ስጠን፣ ከሌሊት ፍርሃት፣ ወደ ጨለማም ከሚወስድ ኃዘን አድነን ከዓመፀኛና ከሐሰተኛ ሰውም ተበዥን ፣ ሰው እንደ መሆናችን የበደልነውን የተሠወረንንም ይቅር በለን፣ አንተ እግዚአብሔር ቸር ሰውን ወዳጅ ነህና፤

በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤

ይ.ሕ. አሜን ፡፡

* * *

ግዕዝ	አማርኛ
ሊጦን ዘቀዳም ሥዑር፣	የቅዳሜ ሥዑር ሊጦን ፣
ትእ. ይሚጥ ካህን ገጸ መንገለ ሕዝብ ወይበል ዘንተ ጸሎተ ሊጦን በልዑል ቃል፣	ትእ. ቄሱ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ ሊጦኑን ሶበ አኮን ከፍ ባለ ድምፅ ይጸልይ ፣
ይ. ካ. ሶበ አኮ እግዚብሔር ምስሌነ፣ ይብል እስራኤል ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ፣ እንተ ጊዜ ተንሥአ ሰብእ ላዕሌነ አሐዝብ ሕያዋኒነ እምውኃጡነ በከመ አንሥኡ ቍጥዐ መዓቶሙ ላዕሌነ፣ አሐዝብ በማይ እምአስጠሙነ፤ እምውኂዝ አምሰጠት ነፍስነ፣ አምሰጠት ነፍስነ እማየ ሐከክ፣ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክነ ዘኢያግብአነ ውስተ መሥገርተ ማዕገቶሙ ነፍስነሰ አምሰጠት ከመ ዖፍ እመሥገርት ነዓዊት፣ መሥገርትሰ ተቀጥቀጠት ወንሕነሰ ድኅነ፣ ረድኤትነሰ በስመ እግዚአብሔር አምላክነ ፤	ይ.ካ. እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ባይኖር ይላል እስራኤል፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ባይኖር ሰው በላያችን በተነሣ ጊዜ በሕይወታችን በዋጡን ነበር ፣ ቍጣቸውን በላያችን እንዳነሡ በውኃ ባሰጠሙን ይመስለኛል፣ ነፍሳችን ከፈሳሽ አመለጠች፣ ነፍሳችን ከክርክር ውኃ አመለጠች፣ በሚከብ ወጥመዳቸው ውስጥ ያላገባን እግዚአብሔር ይመስገን ፣ ነፍሳችን ግን እንደ ዖፍ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች፣ ወጥመድ ተሰበረች፣ እኛም አመለጥን፣ ረድኤታችን ግን ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር ስም ነው፣
ይ. ዲ. ጸልዩ ፣	ይ.ዲ. ጸልዩ ፣
ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣	ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣
ይ. ካ. ዘገብረ ሰማየ ወምድረ፣	ይ.ካ. ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ፣
ዘገብረ ሰማየ ወምድረ፣	ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ፣
ዘገብረ ሰማየ ወምድረ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም፤	ሰማይንና ምድርን የፈጠረ፣ ለዘለዓለሙ ፣
ይ. ሕ. አሜን፡፡	ይ.ሕ. አሜን ፡፡

ግዕዝ

መስተብቍዓን ዘይበቍዑ ለጸሎት በእንተ ኵሉ ግብር

ይ. ካ. ናስተብቍዕ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዘ ነአኵቶ በኵሉ ወበውስተ ኵሉ ፣ እስመ ከደነነ ወረድአነ ሰቀነ ወአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት ንስእል ወናስተብቍዕ፣ ከመ ተረፈ ሌሊትኒ በኵሉ ሰላም ወጥዒና ይረስየነ ዘለምሕረት ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላክነ፣

ይ. ዲ. ጸልዩ፣

ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣

ይ. ካ. እግዚኦ ዘኵሉ ትእኅዝ ንስእል ወናስተብቍዕ ቅዱስ ስመከ፣ ነጽር ላዕሌነ ወውስተ ስእለትነ ሕፅር ሕዝበከ በኃይለ መላእክቲከ ኵሉ ሕመሜ ወኵሉ መንሱተ ደምስስ እምላዕሌየ ወእምላዕለ ኵሉ ሕዝብከ፣ ወተረፈ ሌሊትኒ በኵሉ ሰላም ወዳኅና ጸግወነ ነሀሉ፣

በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣

ይ. ሕ. አሜን፡፡

* * *

መስተብቍዕ በእንተ ዱያን፣

ይ. ካ. ወካዕበ ናስተብቍዖ ለዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ዱያን አኃዊነ፣ ከመ ኵሉ ደቂ ወኵሉ ሕማመ ያስስል እምኔሆሙ መንፈሰ ደቂ ሥዒሮ ሕይወተ የሀቦሙ፣ ዘለኵሉ ፈውስ ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላክነ፣

አማርኛ

ስለ ሥራው ሁሉ ለመለመን የሚጠቅሙ መለመኛዎች ናቸው፣

ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን፤ በውስጥ በአፍኣ እያመሰገነ ስንለምነው ሰውሮናልና፣ ረድቶናልና፣ ደግፎናልና፣ እስከዚችም ሰዓት አድርሶናልና፣ ለምሕረት ሥልጣን ያለው ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሌሊቱን ተረፍ በፍቅርና በጤና ያደርግልን ዘንድ እንለምናለን፤

ይ.ዲ. ጸልዩ ፣

ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣

ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ሆይ ቅዱስ ስምህን እንለምናለን እንማልዳለን ፣ እኛን እይ ወደ ልመናችንም ተመልከት፣ በመላእክት ኃይል ሕዝብህን ጠብቅ ፣ ከእኛ ላይ ከሕዝብህም ላይ ምቀኝነትን ሁሉ ጥፋትንም ሁሉ አጥፋ፣ የሌሊቱንም ተረፍ በፍቅርና በጤና ሁሉ እንኖር ዘንድ መኖርን ስጠን ፣

በክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፣

ይ.ሕ. አሜን ፡፡

* * *

መስተብቍዕ ስለ ሕመምተኞች፣

ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችኃና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ስለ ታመሙ ወንድሞቻችን ዳግመኛ እንማልዳለን ፣ ደዌውን ሁሉ ሕማሙንም ሁሉ ያርቅላቸው ዘንድ፣ የደዌውን መንፈስ አርቆ ሕይወትን ይሰጣቸው ዘንድ፣ ሁሉን ለመፈወስ ሥልጣን ያለው አምላካችን እግዚአብሔር ነው ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ.ዲ. ጸልዩ በእንተ ዱያን፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሉ ትእኅዝ ንስዕለከ ወናስተበቍዓከ ለዱያን አኃው ሕይወተ ሎሙ ጸጉ፣ መንፈሰ ደዌ ሠዓር ኵሉ ደዌ ወኵሉ ሕማመ እምላዕሌሆሙ አኅልፍ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ፣ ይ. ዲ. ንበል ኵልነ ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. መፈውሰ ነፍስ ወመፈውሰ ሥጋ፣ ሐዋዚሃ አንተ ለኵሳ (ሐዋዚሁ አንተ ለኵሉ) ዘሥጋ፣ ወለእለ እምኀበ መናፍስት ርኵሳን ይዜዐሩ አግዕዝ ለኵሳ ነፍስ ምንድብት ወጥውቅት ሀብ ሳኅተ ወሀብ ዕረፍተ ፣ ኵሎ ደዌ ስድድ እምዝንቱ ቤት ወእምእለ ይጼውዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ፣ ወለእለ ጉልቄ ነፍሳቲነ እንከ ደዌ ፈዊስከ ፍጹመ መድኃኒተ ጸጉ፣ በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ ይ. ሕ. አሜን፡፡ መስተብቍዕ በእንተ እለ ይነግዱ፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚ አብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ እለ ይነግዱ አኃዊነ፣ ወበእንተሂ እለ ሀለዉ ይንግዱ፣ እመሂ በባሕር ወእመሂ በአፍላግ ወእመሂ በቀላያት ወእመሂ በፍኖት በዘኮነ መንገደ ይገብሩ ከመ ኵሉ ያብጽሕ ውስተ መርሶ መድኀን ፣ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ ፣	ይ.ዲ. ስለ ሕመምተኞች ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአሔር ሆይ፣ እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለን ፣ ለታመሙት ወንድሞቻችን ሕይወትን ስጣቸው፣ የደዌን መንፈስ አርቅ፣ ደዌውን ሁሉ ሕማሙንም ሁሉ ከእነርሱ አሳልፍ፣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን፣ ይ.ዲ. ሁላችንም እንበል ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር ይበለን ፣ ይ.ካ. ነፍስን የምታድን፣ ሥጋንም የምታድን ፣ ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ የምት ጐበኝ አንተ ነህ ፣ በርኵሳን መናፍስት የሚጨነቁትንም ነፃ አድርግ፣ የተጨነቀችውንና የተቸገረችውን ሰውነት ፍጹም ዕረፍትን ሰጥተህ አሳርፍ፣ ደዌውን ሁሉ ከዚህ ቤት አውጥተህ ስደድ፣ ምስጉን የሚሆን ስምህን ከሚጠሩትም ዘንድ ለየራሳችን ለየቍጥራችን ደዌን አርቀህ ፍጹም ደኅንነትን ስጥ፣ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፣ ይ.ሕ. አሜን ፡፡ መስተብቍዕ ስለ መንገደኞች፣ ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ዳግመኛ እንማልዳለን ፣ መንገድ ስለሚሄዱ ወንድሞቻችን፣ ይነግዱም ዘንድ ስላላቸው ወንድሞቻችን፣ በባሕርም ቢሆን፣ በፈሳሽም ቢሆን በጥልቅም ቢሆን፣ በመንገድም ቢሆን በማንኛቸውም ዓይነት ሆኖ መንገዳቸውን ስለሚያደርጉ፣ ሁሉን ደኅንነት ወዳለበት ወደብ ያደርሳቸው ዘንድ፣ ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ነው ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ.ዲ. ጸልዩ በእንተ እለ ይነግዱ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ ለእለ ነገዱ አኃዊነ፣ ወበእንተሂ እለ ሀለዉ ይንግዱ፣ ለነጊድ አርትዕ ኅቡረ ምስሌሆሙ ከዊነ ፍቅድ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ ፣ ይ. ዲ. ንበል ኵልነ ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. አብጽሖሙ ውስተ ዘመድኅን መርሶ፣ አውፅ ለሰብኦሙ በፍሥሓ ወበኀሤት እንዘ ይትፌሥሑ ወያስተፌሥሑ፣ በፅዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ ይ. ሕ. አሜን፡፡ መስተብቍዕ በእንተ ዝናማት፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ዝናማት ከመ ዝናሞ ይፈኑ ውስተ ኅበ ዘይትፈቀድ መካን ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ዝናማት፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ ዝናማቲከ ፈኑ ውስተ ኅበ ዘይትፈቀድ መካን፣ አስተፍሥሕ ገጻ ለምድር ወአርዊ ትለሚሃ አብጽሕ ለዘርእ ወለ ማዕረር፣ ዘእምኅበ ኂሩትከ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ፤	ይ.ዲ. መንገድ ስለሚሄዱ ሰዎች ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ሆይ መንገድ ለሄዱ ወንድሞቻችን ፣ ይነግዱም ዘንድ ላላቸው እንለምንሃለን፣ እንማልድ ሃለን፣ መንገዱን አቅናላቸው፣ ከነርሱ ጋራ መኖርን ውደድ ፣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን፣ ይ.ዲ. ሁላችንም እንበል ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. ደኅንነት ወደሚገኝበት ወደብ አድርሳቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋራ በተድላ በደስታ ደስ ብሏቸው ደስ አሰኝተው አገናኛቸው ፣ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፣ ይ.ሕ. አሜን ፡፡ መስተብቍዕ ስለ ዝናም ፣ ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ስለ ዝናም ዳግመኛ እንማልዳለን፣ ዝናሙን በሚፈለግበት ቦታ ያዘንምልን ዘንድ፣ ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ነው፣ ይ.ዲ. ስለ ዝናም ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለን፣ ዝናምህን በሚሻበት (በሚፈለግበት) ቦታ አዝንምልን፣ የምድርን ፊትዋን ደስ አሰኛት፣ ትልሚንም አርካ፣ ለዘርና ለአዝመራ አድርስ፣ ከቸርነትህ የተነሣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ንበል ኵልነ ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. በእንተ ነዳያን ሕዝብከ ወበእንተ ኵሎሙ እለ ይሴፈዉከ ግበር ምስሌነ በከመ ምሕረትከ፣ ወሴሲ ልበነ በመለኮተ ትምህርት ወበለብዎ ዘእምኀቤከ፣ በፅዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጎዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን፡፡	ይ.ዲ. ሁላችንም እንበል ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. ስለ ነዳያን ወገኖችህ፣ አንተን ተስፋ ስለሚያደርጉትም ሁሉ ከእኛ ጋራ እንደ ይቅርታህ አድርግ፣ በመለኮታዊ ትምህርትም ልቡናችንን መግብ፤ ከአንተ ዘንድ የሚገኘውንም በማስተዋል ፤ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡
✱ ✱ ✱	✱ ✱ ✱
መስተብቍዕ በእንተ ፍሬ ምድር ፣	**መስተብቍዕ ስለ ምድር ፍሬ፣**
ይ.ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በእንተ ፍሬ ምድር ከመ ፍሬሃ ለምድር ያልህቅ ወያሥምር፣ ያብጽሕ ለዘርእ ወለማዕረር፣ ዘብዑለ ጸጋ ይጼጉ እግዚአ ብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ፍሬ ምድር ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሉ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ ፍሬሃ ለምድር አልህቅ ወአ ሥምር፣ አብጽሕ ለዘርእ ወለማዕረር ዘእምኀበ ኀሩትከ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ፣ ይ. ዲ. ንበል ኵልነ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. በእንተ ነዳያን ሕዝብከ ወበእንተ ኵሎሙ እለ ይጼ ውዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ፣ በፅዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጎዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ ይ. ሕ. አሜን፡፡	ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ስለ ምድር ፍሬ ዳግመኛ እንለምናለን ፣ የምድርን ፍሬ ያሳድግ፣ ያሳምር ዘንድ፤ ለመከርም ያደርሰው ዘንድ ብዙ ጸጋን የሚሰጥ አምላካችን እግዚአብሔር ነው ፣ ይ.ዲ. ስለ ምድር ፍሬ ጸልዩ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለን የምድርን ፍሬ አብዛልን፣ አሳምርልን ለዘርእ ለመከር አድርስልን፣ ከቸርነትህ የተነሣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን፣ ይ.ዲ. ሁላችንም እንበል ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. ስለ ወገኖችህ ስለ ነዳያን ብለህ ክቡር ምስጉን የሚሆን ስምህንም ስለሚጠሩ ሁሉ፣ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡
✱ ✱ ✱	✱ ✱ ✱

ግዕዝ	አማርኛ
መስተብቍዕ በእንተ ማያተ አፍላግ ፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ማያተ አፍላግ ከመ ያዕርግ እስከ መስፈርቶሙ ያስተፍሥሕ ገጾ ለምድር ወያርዊ ትለሚሃ ያብጽሕ ለዘርእ ወለማዕረር ዘብዑለ ጸጋ ይጼጉ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ማያተ አፍላግ ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ ዘአፍላግ ማያተ አዕርግ እስከ መስፈርቶሙ፣ አስተፍሥሕ ገጾ ለምድር ወአርዊ ትለሚሃ አብዝኅ እክለ ወባርክ ዐውደ ዓመት በዘዚአከ ኀሩት፤ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ ፣ ይ. ዲ. ንበል ኵልነ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ ፣ ይ. ካ. በእንተ ነዳያን ሕዝብከ ወበእንተ ኵሎሙ እለ ይጼውዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ፣ በፀዱ ወልድከ ዘበቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፤ ይ. ሕ. አሜን፡፡	መስተብቍዕ ስለ ወንዞች ውኃ ፣ ይ.ካ. ሁሉን የሚችል የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ስለ ወንዞች ውኃ ዳግመኛ እንማልዳለን፣ እስከ ልካቸው ይመላቸው ዘንድ ምድርንም ደስ ያሰኛት ዘንድ ትልምዋንም ያረካው ዘንድ፣ ለዘርና ለመከርም ያደርስ ዘንድ ፣ ብዙ ጸጋን የሚያድል አምላካችን እግዚአብሔር ነው፣ ይ.ዲ. ስለ ወንዞች ውኃ ጸልዩ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ሆይ እንለ ምንሃለን፣ እንማልድሃለን የወንዞችን ውኃ ምች እስከልካቸው ምላቸው ፣ ምድርንም ደስ አሰኛት፣ ትልምዋንም አርካው እህሉንም አብዛ፣ በአንተ ቸርነት ዐውደ ዓመቱን ባርከው ፣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደ ረግልን፣ ይ.ዲ. ሁላችንም እንበል ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. ስለ ወገኖችህ ስለ ነዳያን ብለህ ክቡር ምስጉን የሚሆን ስምህንም ስለሚጠሩ ሁሉ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡
መስተብቍዕ በእንተ ሀገር ፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በእንተ መፍቀሪተ እግዚ አብሔር ሀገሪትነ ኢትዮጵያ ከመ መንግሥታ ዘእንበለ ሕማም በሰላም ወበጽድቅ ይዕቀብ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ፣	መስተብቍዕ ስለ ሀገር ፣ ይ.ካ. ሁሉን የፈጠረ የጌታችን የመድኃኒታ ችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ዳግመኛ እንማልዳለን፣ እግዚአብሔርን ስለ ምትወድ ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያ ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር መንግ ሥቷን ያለሕማም በሰላም በእውነትም ይጠብቅ ዘንድ ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ሀገር፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሉ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ ለመፍቀሪተ እግዚአብሔር ሀገሪትነ ኢትዮጵያ ወባቁዐ ላቲ ጸግዋ አግርር ፀራ አሕዛበ ዘመንገለ ዐረፍታ ወተናገር ጽድቀ ውስቴታ በእንተ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንከ ፍጡነ ይርከባ ሣህልከ እግዚኦ፣ ይ. ዲ. ንበል ኵልነ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃላ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ይ. ካ. ሀባ ዘእንበለ ስሕተት ትዕቀብ ልቡና ዘሃይማኖት ውስተ ሥነ አምልኮትከ፣ በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኊዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፣ ይ. ሕ. አሜን፡፡ * * * መስተብቍዕ በእንተ እለ ኖሙ፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕከ ለዘኵሉ ትእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አምላክ ዘመናፍስት ወለኵሉ ዘሥጋ እግዚአ አጋዕዝት ወአምላከ በቍዔት ዘሞተ አፅራዕከ ወሥልጣኖ ሄድከ ሕይወተ ለትዝምደ ሰብእ ጸኅከ ዘለዕረፍት ሥልጣን ብከ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ እለ ኖሙ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣	ይ.ዲ. ስለ ሀገር ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የያዝህ እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን፤ እንማልድሃለን እግዚአብሔርን ለምትወድ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሚጠቅመውን ነገር ስጣት፣ በዙሪያዋ ያሉ ጠላቶቿን አሕዛብን ከእግረ ሥልጣኗ በታች አስገዛላት፣ ክብርት ስለምትሆን ቤተ ክርስቲያንህ በውስጧ ጽድቅን ተናገር፣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግላት ፣ ይ.ዲ. ሁላችንም እንበል ፣ ይ.ሕ. አገራችን ኢትዮጵያን አቤቱ ይቅር በላት፣ ይ.ካ. ያለ ስሕተት አማኒ ልቡናን ትጠብቅ ዘንድ፣ በበጎ አምልኮትህ አጽናት፤ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ፣ ይ.ሕ. አሜን ፡፡ * * * መስተብቍዕ ስለ ሙታን ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር ሆይ ዳግመኛ እንማልድሃለን፣ የነፍሳትና የሥጋዊ የደማዊ ሁሉ ፈጣሪ፣ የአጋዕዝት ጌታ፣የበረከት ባለቤት፣ ሞትን ያጠፋህ፣ ሥልጣኑንም የቀማኸው፣ ለሰው ወገን ሕይወትን ሰጠህ፣ እረፍትን ለመስጠት ሥልጣን ያለህ አምላካችን አንተ እግዚአብሔር ነህ ፣ ይ.ዲ. ስለ ሞቱ ሰዎች ጸልዩ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሉ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ፣ አምላከ አበዊነ ወአምላከ ቅዱሳን ዕረፍት ለፅዑራን፣ አዕርፍ እግዚኦ ነፍሳተ ጻጻሳቲነ ዕገሌ ወዕገሌ ወኵሎሙ ጳጳሳት እለ አዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት፣ አዕርፍ እግዚኦ ነፍሳተ አግብርቲከ ወአእማቲከ ኵሎሙ ክርስቶሳውያን ውስተ ብሔር ሥዑር ወውስተ መካን ሐዋዝ ኀበ ተኀጥአ ኀዘን ወናዕክ ፣ ወሀብ ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ፣ ወለእለሂ ይላህዉ ናኅየ ወዕረፍተ ጸጉ፣ ለፅዑራን መድኀን ወለነኒ አድኀነነ በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ፤ በኀዱ ወልድከ ዘበቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘ ልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን፡፡	ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ ፈጣሪያችን እግዚ አብሔር ሆይ እንለምንሃለን፣ እንማል ድሃለን፣ የአባቶቻችን አምላክ፣ የቅዱሳንም አምላክ፣ የተጨነቁትን የምታሳርፍ አቤቱ በቀናች ሃይማኖት ሆነው የሞቱ የጳጳሶቻ ችንን፣ የዕገሌንና የዕገሌን የጳጳሳቱንም ሁሉ ነፍሳት፣ አሳርፍ፣ የክርስቶስ ወገን የሆኑትን ሁሉ የወንዶችንም የሴቶችንም ነፍሳት አቤቱ አሳርፍ፣ ልምላሜ ባለበት አገር ባማረ በተወደደ ቦታ፣ የኀዘን ልቅሶ በሌለባት፣ በአብ ርሃም በይስሐቅ፣ በያዕቆብ አጠገብ መኖርን ስጣቸው፣ የተጨነቁትን የምታድን አቤቱ ለሚያለቅሱት ዕረፍትን ስጣቸው ፣ እኛንም በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም አድነን፣ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡
መስተብቍዕ በእንተ ንዑሰ ክርስቲያን፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በእንተ አግብርቲሁ ንዑሰ ክርስቲያን ከመ ይክፍሎሙ በጊዜ ርቱዕ (ርትዕ) ሕፅበተ ዳግም ልደት ለሥርየተ ኃጢአት ፣ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ንዑሰ ክርስቲያን፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣ ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሉ ትእኅዝ ንስ እለከ ወናስተበቍዐከ አግብርቲከ ንዑሰ ክርስቲያን ተሣሃል፣ ኵሉ ተረፈ ጣዖት	መስተብቍዕ ስለ ንዑሰ ክርስቲያን፣ ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ፣ የጌታችንና የመድኃ ኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚ አብሔርን ዳግመኛ ስለ ንዑሰ ክርስቲያን እንለምናለን ኃጢአትን ለማስተሥረይ፣ ዳግም ልደት የሚገኝበትን ሥርየት በሚገባ ይሰ ጣቸው ዘንድ ፣ ሁሉን የሚችል አምላካችን እግዚአብሔር ነው፣ ይ.ዲ. ስለ ንዑሰ ክርስቲያን ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ ፈጣሪያችን እግዚ አብሔር ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለን ፣ አገልጋዮችህን ንዑሰ ክርስቲያንን ይቅር በል፣ የጣዖቱን ቅሬታ ሁሉ ከልቡናቸው

ግዕዝ	አማርኛ
አርኃቅ እምኔሆሙ ፣ ሕገከ ወትእዛዘከ ጽድቀከ ወስምዐከ ሢም ውስተ ሕሊናሆሙ ፣ ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ፣	አርቅላቸው፣ ሕግህንና ትእዛዝህን፣ ጽድቅህ ንና አምልኮትህን በልቡናቸው አሳድርባቸው፣ አቤቱ ይቅርታህ ፈጥኖ ይደረግልን ፣
ይ. ዲ. ንበል ኵልነ ፣	ይ.ዲ. ሁላችን እንበል ፣
ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ ፣	ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣
ይ. ካ. በጊዜ መፍትው ሕፅበተ ዳግም ልደት ለሥርየተ ኃጢአት ማኅፈደ መንፈስ ቅዱስ ረስዮሙ በክርስቶስ ፣	ይ.ካ. የኃጢአት ማስተሥረያ የሚሆን ሁለ ተኛ መወለድ የሚገኝበትን ሥርዮትን በሚገባ አድላቸው፣ በክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አድርጋቸው ፣
ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጊዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣	በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ለአንተ ይገባል፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፣
ይ. ሕ. አሜን ፡፡	ይ.ሕ. አሜን ፡፡
መስተብቍዕ በእንተ ሰላም ፣	መስተብቍዕ ስለ ሰላም ፣
ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ሰላም ለቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተክርስቲያን ከመ ብዙኅ ሰላመ ይጸጉ ላዕለ ኵሉ ሕዝብ ወዲበ ኵሉ መርዔት ዘለኵሉ ሰላም ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላክነ፣	ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንንና የመድ ኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚ አብሔርን ዳግመኛ እንማልዳለን፣ ከሁሉ በላይ ለምትሆን ለከበረች ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን አንድነትን ይሰጣት ዘንድ፣ ለሕዝብም ለምእ መናንም ብዙ አንድነትን ይሰጣቸው ዘንድ ለሁሉ ሥልጣን ያለው አምላካችን እግዚ አብሔር ነው፣
ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ሰላም፣	ይ.ዲ. ስለ ሰላም ጸልዩ ፣
ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣	ትእ.በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣
ይ. ካ. እግዚአብሔር ዘኵሉ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበ ቍዕከ በእንተ ሰላም፣ ንጉሠ ሰላም ሰላመ ሀበነ ፣ እስመ ኵሎ ወሀብከነ፣ አጥርየነ እግዚአብሔር ወዕሥየነ ፣ እስመ ዘእንበሌከ ባዕድ አልቦ ዘነአምር፣ ስመከ ቅዱስ ንሰሚ ወንጼውዕ፣አንተ ዘእምሰማያት ሰላመከ ከልል ላዕለ ዘኵልነ ነፍስ፣ ወንብረተነኒ በዝ ዓለም በሰላም ጸጉ፣	ይ.ካ. ሁሉን የያዝህ እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን፤ እንማልድሃለን ፣ የሰላም ንጉሥ ሆይ አንድነትን ስጠን ፣ ሁሉን ሰጥተኸናልና እግዚአብሔር ሆይ፣ ገንዘብ አድርገን፣ ጸጋህንም ስጠን፣ ከአንተ በቀር ሌላ የምናውቀው የለምና፣ ቅዱስ ስምህን እንጠራለን፣ በሰማይ ያለ ሰላምህን አንተ በሁላችን ሰውነት አሳድር፣ በዚህም ዓለም አኗኗራችንን በሰላም አቅናልን ፣

ዕየዋ

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ሕ. እግዚኦ አምላክነ ሰላመ ሀበነ፣ እግዚኦ አምላክነ ሰላመ ሀበነ፣ ክርስቶስ ንጉሥነ አምላከ ሰላም ተሣሃለነ፤ ይ. ካ. ለመፍቀሪተ እግዚአብሔር ሀገሪትነ ኢትዮጵያ ሰላመ ሀባ በቅዱስ ስምከ፣ ሀብ ምክረ ለመኳንንተ አሕዛብ አግዋረነ በኦተነ ወጸአተነ በሰላም ዕቀብ፣ ከመ በኀዱዕ ወበፅምው ሕይ ወተ እንዘ ነሐዩ በዙሉ አምልኮ ሠናይ በፈሪሀ እግዚአብሔር ወበኂሩት ንትረከብ፣ በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፣ ይ. ሕ. አሜን ፡፡ * * *	ይ.ሕ. አቤቱ አምላካችን ሰላምን ስጠን ፣ አቤቱ አምላካችን ሰላምን ስጠን ክርስቶስ ንጉሣችን ይቅር በለን ፤ ይ.ካ. እግዚአብሔርን ለምትወድ ሀገራችን ኢትዮጵያ በቅዱስ ስምህ ሰላምን ስጣት፣ በዙሪያዋ ላሉ ለአሕዛብ መኳንንትም ምክርን ስጣቸው ፣ በመግቢያችን፣ በመውጫችን ያሉ ጎረቤቶቻችንን በሰላም ጠብቃቸው፣ በቀጥታ በሰላም ሆነን ስንኖር ፍጹም በሚሆን በበጎ አምልኮ እግዚአብሔርን በመፍራትና በቸርነት እንገኝ ዘንድ፣ በክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ለአንተ ይገባል፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፣ ይ.ሕ. አሜን፡፡ * * *

ግዕዝ	አማርኛ
ዘይነግሥ ዘአቡነ ቅዱስ ያሬድ ዘጸዎ ወዘክረምት ወዘአስተምህሮ ፣	የአባታችን የቅዱስ ያሬድ የጾም የክረምትና የአስተምህሮ ዘይነግሥ ፣
ይ. ካ. ወካዕበ ነአኵቶ ወንሴብሖ ለእግዚአ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዓለም ዘይነግሥ ለኵሉ ዘኪያሁ ይሴብሑ ኵሉ ኃይለ ሰማያት ወይዌድስዎ መላእክት ወሊቃነ መላእክት፣ ወለከ ይትቀነዩ ኵሉ ፍጥረት፣ ኪያከ ነአኵት ወኃይለከ ንቄድስ ወለስምከ ንገኒ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ነአኵተከ ወንሴብሐከ በከመ ዐቀብከነ ኑኃ ሌሊት ወአብጻሕከነ ውስተ ብርሃነ መዓልት ብሥዐነ እግዚኦ ዛተኒ ዕለተ በሰላም ወበዳኅና ዕቀበነ ዘእንበለ ኃጢአት ወመንሱት ዘአንተ ሥሉጥ ላዕለ ምሕረት እግዚአብሔር አምላክነ፤	ይ.ካ. የሁሉን ጌታ ዳግመኛ እናመሰግነዋለን፣ እናከብረዋለን፣ አምላካችን ሁሉን የሚይዝ ለሁሉ ነግሦ የሚኖር የሰማዮች ኃይላት የሚያ ከብሩት ሠራዊተ መላእክት ሁሉ መላእክትና የመላእክት አለቆችም የሚያመሰግኑት ነው፣ ፍጥረት ሁሉ ለአንተ ይገዛሉ፣ አንተን እናመሰግናለን ከሃሊነትህንም እናመሰግናለን፣ ለስምህም እንገዛለን፣ በየጊዜው በየሰዓቱም ሁሉ እናመሰግንሃለን፣ እናከብርህማለን፣ ሌሊቱን ሁሉ ጠብቀህ ከመዓልቱ ብርሃን እንዳደረስከን አቤቱ በዚህች ቀንም ተማለደን፣ በፍቅር በደኅንነትም ያለ ኃጢአትና ያለ ፈተና ጠብቀን፣ ይቅርታን ለመስጠት ሥልጣን ያለህ አምላካችን እግዚአብሔር አንተ ነህ፤
ይ. ዲ. ጸልዩ ፣	ይ.ዲ. ጸልዩ ፣
ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣	ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣
ይ.ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ ፣ አምላክ ልዑል፣ አምላክ መሐሪ፣ አምላክ መስተሣህል፣ ርኅቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት ወጸድቅ፣ ነአኵተከ ወንሴብሐከ ዘይሴብሑከ ኵሉ ኃይለ ሰማያት ወይዌድሱከ መላእክት ወሊቃነ መላእክት ወለከ ይገንዩ ኵሉ ፍጥረት ኪያከ ነአኵት ወኃይለከ ንቄድስ ወለስምከ ንገኒ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ነአኵተከ ወንሴብሐከ በከመ ዐቀብከነ ኑኃ ሌሊት ወአብጻሕከነ ውስተ ብርሃነ መዓልት ብሥዐነ እግዚኦ፣ ዛተኒ ዕለተ በሰላም ወበዳኅና ዕቀበነ ዘእንበለ ኃጢአት ወመንሱት፣	ይካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን፣ ልዑል አምላክ፣ መሐሪ አምላክ ይቅር ባይ አምላክ፣ መዓትህ የራቀ ምሕረትህም የበዛ ቸር ነህ፣ እናመሰግንሃለን፣ እናከብርህማለን፣ ሠራዊተ መላእክት ሁሉ የሚያመሰግኑህ፣ መላእክትና የመላእክት አለቆች ሁሉ የሚያ መሰግኑህ ፣ ፍጥረቱ ሁሉ ለአንተ የሚገዙ፣ አንተን እናመሰግናለን ፣ ለከሀሊነትህም ምስጋናን እናቀርባለን፣ ለስምህም እንገዛለን፣ በየጊዜው በየሰዓቱም ሁሉ እናመሰግንሃለን፣ እናከብርህማለን፣ መላ ሌሊቱን ጠብቀህ ከመዓልቱ ብርሃን እንዳደረስከን አቤቱ ተማለደን፣ በዚችም ቀን ሁሉ ያለ ኃጢአትና ያለ ክሕደት በሰላምና በሕይወት ጠብቀን ፣
በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤	በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ
ይ. ሕ. አሜን ፡፡	ይ.ሕ. አሜን ፡፡

ግዕዝ	አማርኛ
ዘይነግሥ በእንተ ዱያን ፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚአ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋዊሃ ለነፍስ ወመፈውሰ ሥጋ ዘያወርድ ውስተ ሲኦል ወካዕበ ያዐርግ ዘይፈውስ ቅጥቃጤሃ ለነፍስ፣ በእንተ ኵሎሙ ዱያን ፣ ከመ ኵሎ ይፈውስ ወያንሥእ፣ ዘውእቱ ሥሉጥ ላዕለ ምሕረት እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ ዲ. ጸልዩ በእንተ ዱያን፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣ ይ. ካ. እወ እግዚአ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለዋሕድ (ለቅዱስ) ወልድከ እግዚእነ አኃዊነ ዱያነ ፈውስ ወለእለሂ አኃንንተ አውፅእ ወለእለሂ አርኃቁ ደዊ ናዝዝ ሕማማ ለነፍስ ሐውፅ ወኵሉ ፈውስ እስመ ትክል ወጽኑዕ አንተ ዘትገብር መድምመ፣ ይ. ዲ. ተሣሃለነ ፣ ይ. ሕ. እግዚአ ተሣሃለነ ፣ ይ. ካ. ዘ፱ ወ፯ተ ክረምተ መፃጉዕ አሕዮከ ወአልዓዛርሃ እሙታን አንሣእከ ወለዘ፩ዱ ለእሙ ጸጎከ ወለዘእንተ ደም ይውኃዛ አሕዮከ ወለሐማተ ጴጥሮስ እምፈጸንታ አንሣእከ ከማሁ ዲበ እሉኒ ዱያን ግበር ትእምርተ ዘሠናይ ወፈኑ ላዕሌሆሙ ነጠብጣበ ምሕረትከ እስመ ጠል ዘእምኀቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ ከመ እሙ ንቱሂ ተንሢኦሙ ይሰብሑከ ምስሌነ ወና ልዕል ስመከ ኀቡረ፣ በዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለኮት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን ።	ዘይነግሥ ስለ ዱያን ፣ ይ.ካ. የሁሉን ጌታ አምላካችንን ዳግመኛ እንማልደዋለን፣ ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነፍስን የሚጐበኛት ሥጋንም የሚያድን፣ ወደ ሲኦል የሚያወርድ፣ ዳግመኛ የሚያወጣ ፣ ሕማመ ነፍስን የሚ ያድን፣ ስለ ዱያን ሁሉ፣ ሁሉንም አድኖ ያስነሣ ዘንድ፣ ይቅርታን ለማድረግ ሥልጣን ያለው አምላካችን እግዚአብሔር ነው ፣ ይ.ዲ. ስለ ዱያን ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. አቤቱ አምላካችን ሁሉን የያዝህ፣ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የቅዱስ ልጅህ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ ወንድ ሞቻችን ድውያንን አድን፣ ያደሩባቸውንም አጋንንት አውጣ፣ በደዌ የተለዩትንም አረጋጋ፣ የታመመችውን ሰውነት ጐብኝ፣ ሁሉንም አድናቸው፣ ይቻልሃልና፣ ድንቅ ተአምራትን የምታደርግ አንተ ጽኑ ነህና፣ ይ.ዲ. ይቅር በለ ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን፣ ይካ. ፴፰ ዓመት ታሞ የነበረውን መፃጉዕን አዳንህ፣ አልዓዛርንም ከሙታን አስነሣህ፣ ለእናቱ አንድ የነበረውንም ሰጠህ፣ ደም ይፈሳት የነበረችዩቱን አዳንህ፣ ሐማተ ጴጥሮስን ከሆድ ዝሚያዋ አስነሣሃት እንደዚሁም ሁሉ በነዚህ በሽተኞች ላይ በጎ አምልኮትን አድርግ፣ ነጠብጣበ ምሕረትህንም በነሱ ላይ አውርድ፣ ከአንተ የሚገኝ ጠል ሕይወታቸው ነውና፣ እነሱም ተነሥተው ከእኛ ጋራ ያመሰግኑህ ዘንድ፣ ስምህንም በአንድነት ከፍ ከፍ እናደርግ ዘንድ፣ በአንድ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ግዛት ጌትነት ያለህ፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለ ዓለሙ፣ ይ.ሕ. አሜን ።

ግዕዝ	አማርኛ
ዘይነግሥ በእንተ እለ ይነግዱ፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚአ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዘይሁብ ፍኖተ ባሕር ወውስተ ማይ ኃያል ምሕዋረ፣ ዘያወፅኦሙ እመዛግብቲ ሞሙ ለነፋሳት፣ በእንተ ኵሎሙ እለ ይነግዱ እለ በኵለሄ ወበኵሉ ለእለሂ ውስተ ባሕር ወለእለሂ ውስተ አፍላግ ወለእለሂ ውስተ በድው ናስተቍዐከ፣ ከመ ለኵሎሙ ታብጽሖሙ ውስተ አብያቲሆሙ ዘበፍሥሓ እንዘ ይትፌሥሑ ወያስተፌሥሑ ዘላዕለ ኵሉ ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ እለ ይነግዱ፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣ ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ኵሎሙ እለ ይነግዱ እለ ዘበእንቲአሆሙ ንስእል ወናስ ተበቍዕ ንስእለከ ፣ ከመ ለኵሎሙ ትኩኖሙ መርሐ፣ ይ. ዲ. ተሣሃለነ ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. ለእለሂ ይነግዱ ንግድ ምስሌሆሙ ወለእለሂ በእግር የሐውሩ ሑር ምስሌሆሙ፣ ወለእለሂ ይትመነደቡ አብጽሖሙ ውስተ መርሶ መድኃኒት ለእለሂ ይሳኩዩ ምርሖሙ ፍኖተ ጽድቅ፣ ወለእለሂ እለ ሀለው ለነጊድ ዕቀቦሙ ዘእንበለ ማዕቀፍ ሀቦሙ ሥርዓተ መንገዶሙ ለኵሎሙ እለ ዘበእንቲአሆሙ ንስእል ወናስተበቍዕ ሠርሖሙ፣ ከመ አንተ በእሉኒ ወከመ በኵሉ ይሰባሕ ስምከ ቅዱስ፣	ዘይነግሥ መንገድ ስለሚሔዱ፣ ይ.ካ. የሁሉን ጌታ አምላካችንን ዳግመኛ እን ማልደዋለን፣ ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ የባሕር ጎዳናን የሚሰጥ በፈሳሽ ውሃም መንገድን የሚሰጥ፣ ነፋሳትን ካሉበት የሚያወጣቸው፣ በዐራቱ መዓዝን መንገድ ስለሚሔዱ በባሕር ስላሉት፣ በፈሳሽ ውሃም ስላሉት፣ በበረሃም ስላሉት ሁሉ እንማልድሃለን፣ ሁሉንም ወደ ቤታቸው በደስታ ደስ እያላቸው ደስ እያሰኙ ታደርሳ ቸው ዘንድ፣ በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው አምላካችን እግዚአብሔር ነው፣ ይ.ዲ. መንገድ ስለሚሄዱ ሰዎች ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን ሁሉን የያዘ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታ ችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሆይ ስለነርሱ የምንለምንና የምንማልድ መን ገደኞች ሁሉ ናቸው፣ ለሁሉም መሪ ትሆናቸው ዘንድ እንለምንሃለን፤ ይ.ዲ. ይቅር በለን ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. መንገድ ከሚሔዱ ሰዎች ጋራ ሂድ፣ በየብስ ከሚሄዱም ጋራ ሂድ፣ የሚጨነቁትንም ደኅንነት ወዳለበት ወደብ አድርሳቸው፣ የሚቅበዘበዙትን እውነተኛን መንገድ ምራ ቸው፣ በመንገድ ያሉትን ያለ እንቅፋት ጠብቃቸው፣ የሚገባውን መንገድ ምራቸው፣ ስለነርሱ የምንለምንላቸውን የሁሉንም አከናውንላቸው፣ አንተ እንደ መሆንህ በእነዚ ህም በሁሉም ቅዱስ ስምህ ይመሰገን ዘንድ ፣

ግዕዝ	አማርኛ
በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለኮት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን *** ዘይነግሥ በእንተ ዝናማት፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚአ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚኦሙ ወአምላኮሙ ለማያት ኀስእለከ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፈኑ ዝናመ ውስተ ፍና ኀበ ይትፈቀድ፣ አስተፍሥሕ ገጻ ለምድር ወአርዊ ትለሚሃ ወበነጠብጣብከ ትበቍል ተፈሢሓ ሀባ ለምድር ዘርአ ወማዕረረ ወለአፍላግኒ ምላዕ ማያተ በመዋዕለ ጊዜሁ ፍጹም ፣ ዘላዕለ ኵሉ ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላክነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ዝናማት፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣ ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚኦሙ ወአምላኮሙ ለማያት ኀስእለከ ወናስ ተበቍዐከ በእንተ ዝናማት ከመ ተሀበነ ማያተ ወትምላዕ አፍላገ አስተፍሥሕ ገጻ ለምድር ወአርዊ ትለሚሃ ሀባ ፍሬ ለዘርእ ወለ ማዕረር ወባርክ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ በእንተ ነዳያን ሕዝብከ ወበእንተ ኵሎሙ እለ ይሴፈዉከ ወኵሎ መካነ ኀበ ይትፈቀድ ሀብ ጸጋከ፣	በልጅህ በወዳጅህ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ግዛት ጌትነት ያለህ፣ ዛሬም ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ ፤ ይ.ሕ. አሜን ። *** ዘይነግሥ ስለ ዝናማት ፣ ይ.ካ. የሁሉን ጌታ አምላካችንን ዳግመኛ እንማልደዋለን፣ ሁሉን የያዘ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ የማያት (የውሀዎች) ጌታቸውና አምላካቸው ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለን፣ ወደሚሻበት መንገድ ዝናምን ትልክልን ዘንድ የምድርን ፊት ደስ አሰኝ፤ ትልሚንም አርካ ፣ ከላይ ነጠብጣብህን ተቀብላ ደስ ብሏት ዘርን ታበቅላለች፤ ለምድር ዘርን መከርን ስጣት፣ አፍላግም (ወንዞችም) በሚመሉበት ወራት ጊዜ በውኃ እንዲመሉ አድርግ፣ በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው አምላካችን እግዚአብሔር ነው ፣ ይ.ዲ. ስለ ዝናማት ጸልዩ ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣ ይ.ካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን፤ ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የማያት ጌታቸውና አምላካቸው ስለ ዝናማት እንለምንሃለን ፣ እንማልድሃለን፣ ውኃውን ትሰጠን ዘንድ፣ ወንዙንም ትመላ ዘንድ፣ የምድርን ፊቷን ደስ አሰኝ፣ ትልሚንም አርካ፣ ለዘር ለመከር እንዲሆን ፍሬን ስጣት፣ በምሕረትህ ዘመን የተገኘውን ምርቱን ባርክ፣ ስለ ድኖች ሕዝቦችህ ተስፋ ስለሚያደርጉህም ሁሉ ሰው ከሚፈልገውም ሁሉ ጸጋህን ስጥ ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ተሣሃለነ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ ፣ ይ. ካ. አዝዞሙ ለደመናት ያውርዱ ዝናመ ዘቀዳሚ ወዘደኃሪ መሐር አግብርቲከ ወአእ ማቲከ ወተመየጥ ነዳያነ ወምስኪናነ ዕቤራተ ወዕጓለማውታ እስመ ኵሎሙ ኀቤከ ይጸርሑ ኪያከ መሴስየ ኵሉ ይትመሀለሉ ወይስእሉ ኪያከ መጋቤ ኵሉ፣ ኵሎሙ ተሣሃል ወአጽግብ ከመ ይክሀሉ ዘበሥጋ ወዘበመንፈስ ዘልፈ ሰብሖተከ ፣ በዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለኮት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን ።	ይ.ዲ. ይቅር በለን ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. ደመናትን እዘዛቸው፤ የኋለኛውንና የፊተኛውን ዝናም ያወርዱ ዘንድ ወንዶችና ሴቶች ባሮችህን ይቅር በላቸው፤ ወደ ድኆችና ወደ ምስኪናን ወደ ባልቴቶችና አባት እናት ወደሌላቸው በይቅርታ ተመለስ፣ ሁሉም ወደ አንተ ይጮኃሉ፣ ሁሉን ወደ ምትመግብ ወደ አንተ ይጸልያሉና፣ ለሁሉም ምግብን ወደምትሰጥ ወደ አንተ ይለምናሉና፣ ሁሉን ይቅር በል፣ አጥግብም በሥጋ በነፍስ የተፈጠሩ ሁሉ ዘወትር አንተን ማመስገን ይቻላቸው ዘንድ ፤ በአንድ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ግዛት ጌትነት ያለህ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ፣ ይ.ሕ. አሜን ።
## ዘይነግሥ በእንተ ፍሬ ምድር፣	## ዘይነግሥ ስለ ምድር ፍሬ ፣
ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚአ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በእንተ ፍሬ ምድር ከመ ፍሬሃ ለምድር ያልህቅ ወያሥምር ወይዕቀብ ዘእንበለ ሙስና መሴስየ ኵሉ ዘሥጋ ዘብዑለ ጸጋ ይጼጉ እግዚአብሔር አምላክነ ። ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ፍሬ ምድር፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣	ይ.ካ. የሁሉን ጌታ አምላካችንን ሁሉን የሚይዝ ለዓለም ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ስለ፣ ምድር ፍሬ ዳግመኛ እንማልደዋለን፣ የምድርን ፍሬ ያሳድግ ያበጅ ዘንድ፣ ያለጥፋትም ይጠብቅ ዘንድ ሥጋዊ ደማዊውን ሁሉ የሚመግብና ሀብተ ጸጋን የሚሰጥ አምላካችን እግዚአብሔር ነው። ይ.ዲ. ስለ ምድር ፍሬ ጸልዩ፣ ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣
ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይ ነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ በእንተ ፍሬ ምድር፤ ፍሬሃ ለምድር አልሕቅ ወአሥምር ወዕቀብ ዘእንበለ ሙስና እግዚአብሔር አምላክነ፣	ይ.ካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን፤ ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ ስለ ምድር ፍሬ እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለን ፣ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፣ የምድርን ፍሬ አሳድግ፣ አብጅ፣ ያለጥፋትም ጠብቅ ።

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ተሣሃለነ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ ፣ ይ.ካ.እስመ አንተ ዘታሠርፅ ሣዕረ ለእንስሳ ወሐ መልማለ ለቅኔ ዕጓለ እመሕያውከ እስመ ዓይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ አንተ ትሁቦሙ ሲሳዮሙ በጊዜሁ፣ ትሰፍሕ የማነከ፣ ወታ ጸግብ ለኵሉ እንስሳ ዘበሥርዓትከ ፣ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለኮት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፤ ይ. ሕ. አሜን ፡፡	ይ.ዲ. ይቅር በለን ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፣ ይ.ካ. ለእንስሳ ሣርን የሰው ልጅም አንተን ያመስግን ዘንድ ልምላሜውን የምታበቅል አንተ ነህና ፣ የፍጥረት ሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋልና፣ በጊዜው ጊዜ ምግባቸውን አንተ ትሰጣቸዋለህ ፣ ቀኝህን ዘርግተህ በሥርዓትህ ያሉ እንስሳትን ሁሉ ታጠግባለህ፣ በተወደደ ልጅህ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ግዛት ጌትነት ያለህ፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ፣ ይ.ሕ. አሜን ፡፡

* * *

ዘይነግሥ በእንተ ማያተ አፍላግ፣

ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚኦ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ማያተ አፍላግ፣ ከመ ያዕርግ እስከ መስፈርቶሙ፤
እስመ አንተ ዘትገብር ሠናያተ ወታርጉ ክረምተ ወትፌኑ ዝናማተ ፣ አስተፍሥሕ ገጸ ለምድር ወአርዊ ትለሚሃ፣ አብጽሕ ለዘርእ ወለማዕረር ዘሥሉጥ እንተ ላዕለ ምሕረት እግዚአብሔር አምላክነ፣
ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ማያተ አፍላግ፣
ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት፣

ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣

ንስእለከ ወናስተበቍዐከ በእንተ ማያተ አፍላግ፤ ዘአፍላግ ማያተ አዕርግ እስከ መስ ፈርቶሙ አዝዘሙ ለደመናት ያውርዱ ዝናመ ወምልዖሙ ለአፍላግ ማያተ በዐቅሞሙ፣ በጊዜ መፍትው አስተፍሥሕ ገጸ ለምድር ወአርዊ ትለሚሃ አብዝኃ እክለ፤ ወባርክ ዐውደ ዓመት በዘዚአከ ኂሩት፡፡

ይ.ካ. የሁሉን ጌታ አምላካችንን ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስ ቶስን አባት ስለ ወንዞች ውኃ ዳግመኛ እንማልደዋለን፤ እስከልካቸው ድረስ ይመላ ቸው ዘንድ ፣
በጎውን የምታደርግ አንተ ነህና ክረምትን የምታመጣ ዝናሙንም የምታዘንም፣ የምድርን ፊት ደስ አሰኝ፤ ትልሚንም አርካ፣ ለዘር ለመከር አብቃት፣ ይቅርታን ለማድረግ ሥልጣን ያለህ አምላካችን እግዚአብሔር አንተ ነህ ፣
ይ.ዲ. ስለ ወንዞች ውኃዎች ጸልዩ ፣
ትእ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣
ይ.ካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ፤
ስለ ወንዞች ውኃዎች እንለምንሃለን፤ እንማልድሃለን፣ የወንዞችን ውኃዎች እስከ ልካቸው ድረስ አውጥተህ ምላቸው፣ ደመና ዎች ዝናሙን ያወርዱ ዘንድ እዘዛቸው፤ ወንዞችንም ውኃን በልካቸው ምላቸው ፣ በሚገባው ጊዜ የምድርን ፊት ደስ አሰኝ፣ ትልሚንም አርካ ፤ እህሉን አብዛ፤ የዓመቱ ንም በዓል በአንተ ቸርነት ባርክ ፤

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ተሣሃለነ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ ፤ ይ. ካ. እስመ አንተ ዘትገብር ሠናያተ ወታርጉ ክረምተ ፤ ወትፌኑ ዝናማተ ዲበ ገጸ ለምድር በእንተ አትክልት ወጽጌያት ወፍሬያተ ምድር፣ እስመ አንተ መሴስይ ለኵሉ ዘሥጋ ወለከ ይደሉ ስብሐት ምስለ ወልድከ ፍቁርከ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለኮት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፤ ይ. ሕ. አሜን ።	ይ.ዲ. ይቅር በለን ፤ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ፤ ይ.ካ. በጎውን የምታደርግ ክረምትንም የምታመጣ አንተ ነህና፤ ስለ አታክልትና ስለ አበባ ስለ ምድር ፍሬም በምድር ላይ ዝናሙን የምታዘንም አንተ ነህና፣ ሥጋዊ ደማዊን ሁሉ የምትመግብ አንተ ነህና፣ ከልጅህ ከወዳጅህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ ምስጋና ለአንተ ይገባል፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ግዛት ጌትነት ያለህ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፣ ይ.ሕ. አሜን ።
ዘይነግሥ በእንተ ሀገር፣ ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚኦ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እግዚኦሙ ለአጋዕዝት ወንጉሠሙ ለነገሥት በእንተ መፍቀሪተ እግዚአብሔር ሀገሪትነ ኢትዮጵያ ከመ መንግሥታ ይዕቀብ በጽድቅ ወበሰላም መዋዒ በኵሉ ፀብዕ እግዚአብሔር አምላክነ፤ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ሀገር፣ ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፤ ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚኦሙ ለአጋዕዝት ወንጉሠሙ ለነገሥት ንስእለ ወናስተበቍዐከ በእንተ መንግሥተ ሀገርከ መፍቀሪተ እግዚአብሔር ሀገሪትነ ኢትዮጵያ በሰላም ወበጽድቅ ዕቀብ ከመ ብንተ ዓይን ወበጽላሎተ ክነፊከ ክድን ፤	ዘይነግሥ ስለ ሀገር ፤ ይ.ካ. የሁሉን ጌታ አምላካችንን ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የገዢዎች ገዥያቸው የንጉሦች ንጉሣቸው የሚሆን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት፣ ዳግመኛ እንማልደዋለን፣ እግዚአብሔርን ስለምትወድ ስለሀገራችን ኢትዮጵያ መንግሥት እንለምናለን፣ መንግሥቷን በዕውነትና በሰላም ይጠብቅ ዘንድ በሰልፍ ሁሉ ድል የሚያደርግ አምላካችን እግዚአብሔር ነው ። ይ.ዲ. ስለ ሀገር ጸልዩ ፤ ት እ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ ፤ ይ.ካ. እውነት ነው አቤቱ አምላካችን ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የገዢዎች ገዢያቸው ፤ የነገሥታት ንጉሣቸው ሆይ እግዚአብሔርን ስለምትወድ ስለ ሀገራችን ኢትዮጵያ መንግሥት እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለን፣ በሰላምና በዕውነት ጠብቀው፣ እንደ ዓይን ብሌን በክንፍህም ጥላ ሠውረው።

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ተሣሃለነ ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃላ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ፣ ይ. ካ. አግርር ላቲ ፀራ ታሕቴሃ ብዙኃ ሰላመ ጸግዋ በኵለሄ ወበኵሉ በሐውርት ለብዙኃ መዋዕል ወለጕንዱይ ዓመታት ወለነዋኅ ክራማት ለተድላ ወለዳኅና ዚእነ ወስካ አሚነ ወሃይማኖተ ተናገር ውስቴታ በእንተ አብያተ ክርስቲያናቲከ ሀባ ሰላመ በእንቲእነ ወበእንተ ኵሉ ሕዝብከ ከመ ንሕነኒ ዕሩፈ ነሀሉ በሰላም ወንሕየው በፈሪሃ እግዚአብሔር ወበኂሩት ንትረከብ ፣ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለኮት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን ።	ይ.ዲ. ይቅር በለን ፣ ይ.ሕ. አቤቱ ሀገራችን ኢትዮጵያን ይቅር በላት ፣ ይ.ካ. ጠላቷን ከበታችዋ በታች አስገዛላት፣ በአራቱም መዓዝን በአውራጃው ሁሉ ብዙ ሰላምን ስጣት፣ ለብዙ ወራት ለረጅም ዘመናት ለሰፊ ክረምት ለእኛ ደስታና ደኅንነት ማመንን ሃይማኖትንም ጨምርላት፣ በውስጧ አድረህ ስለቤተ ክርስቲያንህ ተናገር፣ ሰላምን ስጣት፣ ስለ እኛና ስለ ወገኖችህ ሁሉ በሰላም ዐርፈን እንኖር ዘንድ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት እንኖር ዘንድ በበጎነትም እንገኝ ዘንድ ፣ በተወደደ ልጅህ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ፣ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ግዛት ጌትነት ያለህ፣ ዛሬም ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ ፣ ይ.ሕ. አሜን ።

ዘይነግሥ በእንተ ሰላም ፣

ይ. ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለእግዚኦ ኵሉ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በእንተ ሰላም ለቅድስት አሐቲ እንተ በኵለሄ ቤተ ክርስቲያን ከመ ብዙኃ ሰላመ ይጸጉ ላዕለ ኵሎሙ ኖሎት ወአሕዛብ፣
ውእቱ ወሀቤ ሰላም እግዚአብሔር አምላክነ ፣
ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ሰላም፣
ትእ. በዝየ ይበሉ ሕዝብ አቡነ ዘበሰማያት ፣
ይ. ካ. እወ እግዚኦ አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘይነግሥ ለኵሉ ዓለም አቡሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ንስእለከ ወናስተበቍዓከ በእንተ ሰላም ንጉሠ ሰላም ሰላመ ሀበነ እስመ ኵሉ ወሀብከነ አጥርየነ እግዚአብሔር ወዕሥየነ እስመ ዘእንበሌከ ባዕድ አልቦ ዘነአምር ስመከ ቅዱሰ ንሰሚ ወን ጼውዕ አንተ ዘእምሰማያት ሰላመከ ፈኑ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ፣ | ይ.ካ. ስለ ሰላም ጸልዩ ፣
ት እ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልዩ፣
ይ.ካ. እውነት ነው፣ አቤቱ አምላካችን፣ ሁሉን የሚይዝ ለዓለሙ ሁሉ ነግሥ የሚኖር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ ስለ ሰላም እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለን፣ የሰላም ንጉሥ ሆይ ሰላምን ስጠን፣ ሁሉን ሰጥተኸናልና፣ እግዚአብሔር ሆይ ገንዘብ አድርገን፣ ዋጋችንንም ስጠን፣ ከአንተ በቀር ሌላ የምናውቀው የለምና፣ ቅዱስ ስምህን ፈጽመን እንጠራለን ፣ ከሰማይ የሚገኝ ሰላምህን በሁላችን ልቡና ላክ፣ |

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ዲ. ተሣሃለነ ፣ ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ፣ ይ. ካ. ወንብረተነኒ በዝ ዓለም በሰላም ዕቀብ ወለመንግሥተ ዛቲ ምድር ሰላመ የሃሊ በእንቲአነ ወበእንተ ኵሉ ሕዝብከ መኳንንተኒ ወአሕዛብ አግዋረነ በአተነ ወጸአተነ በሰላም ዕቀብ ከመ በዳኅና ወበዕረፍት ሕይወተ እንዘ ነሐዩ በኵሉ አምልኮ ሠናይ በፈሪሃ እግዚአብሔር ወበኂሩት ንትረከብ ፣ በዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወመለከት ወክብር ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፤ ይ. ሕ. አሜን ፡፡ ካልዓት መስተብቍዓት፣ መስተብቍዕ በእንተ ሙታን፣ ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሉ ይእኅዝ እግዚአ ብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ እለ ኖሙ አበዊነ ከመ ነፍሶሙ ያግዕዝ ውስተ መካን ሥዑር ወኅበ ማየ ዕረፍት ወያኅብር አንሥአ ሥጋሆሙ በዘባቲ ሠርዐ ዕለተ በዘኢይትሔሰው ተስፋሁ ዘበሰማያት መንግሥተ ይክፍል፣ በእንተ ነፍሰ ገብሩ እኁነ ዕገሌ፣ በእንተ ነፍሰ ገብሩ እኁነ ዕገሌ፣ በእንተ ነፍሰ ገብሩ እኁነ ዕገሌ፣ ዘለዕረፍት ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላከነ፣ ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ እለ ኖሙ፣ ይ. ሕ. መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣ መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ ፣ መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ ፣	ይ.ዲ. ይቅር በለን፣ ይ.ሕ. አቤቱ ይቅር በለን፣ ይ. ካ. በዚህ ዓለም የሚሆን አነዋ ወራችንንም በሰላም ጠብቅ፣ የዚህች ሀገር መንግሥት ሰላምን ያስብ ዘንድ ስለእኛ ስለ ሕዝብህም ሁሉ፣ መኳንንቱንም አሕዛብንም ጎረቤቶቻችንን በምንገባበት በምንወጣበት ጊዜ በሰላም ጠብቀን፣ በደኅንነትና በዕረፍት እየኖርን በፍጹም በጎ አምልኮ እግዚአብሔርን በመፍራትና በቸርነት እንገኝ ዘንድ ፣ በአንድ ልጅህ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ጌትነት ክብር ያለህ፣ ዛሬም ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡ ሌሎች መስተብቍዖች ፣ መስተብቍዕ ስለ ሙታን ፣ ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ስለ ሞቱት አባቶቻችን ዳግመኛ እንማልዳለን፣ በለመለመ ቦታና የዕረፍት ውኃ ባለበት ነፍሳ ቸውን ነፃ ያደርግ ዘንድ፣ ትንሣኤን በሠራባት ቀን ሥጋቸውን ማስነሣትን ያስተባብር ዘንድ፣ በማይታበል ተስፋው መንግሥተ ሰማያትን ያድል ዘንድ ፣ ስለ አገልጋዩ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምናለን ፣ ስለ አገልጋዩ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምናለን ፣ ስለ አገልጋዩ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምናለን ፤ ዕረፍትን ለመስጠት ሥልጣን ያለው አምላካችን እግዚአብሔር ነው ፣ ይ.ዲ. ስለ ሞቱ ሰዎች ጸልዩ፣ ይ.ሕ. አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣ አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣ አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ካ. እግዚአብሔር አምላክነ ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ በእንተ እለ ኖሙ አበዊነ ከመ ነፍሶሙ ታግዕዝ ውስተ መካን ሥዑር ወነበ ማየ ዕረፍት ወታኅብር አንሥኦ ሥጋሆሙ በዘባቲ ሠራዕከ ዕለተ በዘኢይትሔሰው ተስፋከ ዘበሰማያት መንግሥ ተከ ክፍል፣	ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ስለ ሞቱት አባቶቻችን እንለምንሃለን ፣ እንማ ልድሃለን፣ በለመለመ ቦታና የዕረፍት ውኃ ባለበት ነፍሳቸውን ነፃ ታደርግ ዘንድ ትንሣኤን በሠራህባት ቀን ሥጋቸውን ማስነሣትን ታስተባብር ዘንድ፣ በማይታበል ተስፋህ መንግሥተ ሰማያትን ዐድል ፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምናለን ፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምናለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምናለን፤
ይ. ሕ. መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	ይ.ሕ. አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ ፣	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ ፤	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፤
ይ. ካ. ማኅለፍታተ ነፍሶሙ ግዑዝ ዘእንበለ ክልኣት ወዘእንበለ ሕመሜ ጸጉ በጊዜ መፍትው ሥጋ አኅቢረከ አንሥእ ዘበሰማያት መንግሥተ ክፍሎ፤	ይ.ካ. የነፍሳቸውን መንገድ ነፃ አድርገህ ያለ መከልከልና ያለ ምቀኝነት በሚገባው ጊዜ ስጣ ቸው፣ ሥጋቸውን ከነፍሳቸው ጋራ አስተ ባብረህ አስነሣ ፣ መንግሥተ ሰማያትን ዐድለው፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን ፤
ይ. ሕ. መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	ይ.ሕ. አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ ፣	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ ፣	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣
ይ. ካ. ወእንዘ ተዐሢ ዕሤተ ሠናየ ዘዓይን ኢርእየ ወእዝን ኢሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ፣ ወኢዐርገ መጠነ አስተዳሎከ አንተ እግዚአ ብሔር ለእለ ያፈቅሩከ ፣	ይ.ካ. ዓይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን፣ በሰው ልብ ያልታሰበውን በጎ ዋጋ ሰጥተህ፣ አንተ እግዚአብሔር ሊ.ሚወዱህ እንደ አዘጋጀህላቸው መጠን ፣
መናኅየ ወመናዝዘ ለሰብኦሙ ፈኑ፣	የሚያሳርፍና የሚያረጋጋን ለሰዎቻቸው ላክ፣
መናኅየ ወመናዝዘ ለሰብኦሙ ፈኑ፣	የሚያሳርፍና የሚያረጋጋን ለሰዎቻቸው ላክ፣
መናኅየ ወመናዝዘ ለሰብኦሙ ፈኑ፣	የሚያሳርፍና የሚያረጋጋን ለሰዎቻቸው ላክ፣
ከዊነከ ክፍል፣ በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኁዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤	ጠባቂ ሆነህ ዐድል ፣ በክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤
ይ. ሕ. አሜን፡፡	ይ.ሕ. አሜን ፡፡

ግዕዝ	አማርኛ
ዓዲ መስተብቍዕ በእንተ ሙታን፣	ዳግመኛ መስተብቍዕ ስለ ሙታን ፤
ይ. ካ. ወካዕበ ናስተብቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣	ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን ዳግመኛ እንማልደዋለን ፤
እግዚአ ሕያዋን ሕይወተ ሙታን ተስፋ ቅቡዓን ረዳኤ ምንዱባን ወመንጽሔ ኃጥኣን፣	የሕያዋን ጌታ የሙታን ሕይወት፣ ተስፋ ለቈረጡት አለኝታ፣ የተቸገሩትን የሚረዳ፣ ኃጥአንን የሚያነጻ፣
ዘሞተ አፀራዕከ ወማዕሠረ ሰይጣን በቲከከ ሕይወተ ለትዝምደ ሰብእ ጸጎከ፣ ኀቤከ ንስእል ወናስተብቍዕ ዘኢትመውት ለዓለመ ዓለም፣ ዘመዝገበ ሕይወት ኀቤከ ውእቱ፣	ሞትን ያጠፋህ የሰይጣንን ወጥመድ ቈርጠህ ለሰው ትውልድ ሕይወትን የሰጠህ፣ አቤቱ ወደ አንተ እንለምናለን፣ እንማልዳለን ፤ ለዘለዓለም የማትሞት ነህ፣ የሕይወት ሣጥንም በአንተ ዘንድ ነው፣
በእንተ እለ ኖሙ በሃይማኖት ወአዕረፉ አበው ቀደምት ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት አናጉንስጢስ ወመዘምራን ደናግል ወመነኮሳት፣ ሕፃናት ዕቤራት ወዕጓለ ማውታ፣	በሃይማኖት ስለ ሞቱ ስለ ቀደሙ አባቶች ስለ ጳጳሳት አለቆችና ስለ ኤጲስቆጶሳት፤ ስለ ቀሳውስትና ስለ ዲያቆናት፣ ስለ አንባቢዎችና ስለ መዘምራን ስለ ደናግልና ስለ መነኮሳት፣ ስለ ሕፃናት ስለ ባልቴቶችና አባት እናት ስለሌላቸው ፤
በእንተ ነፍሰ ገብሩ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋዩ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ ፤
በእንተ ነፍሰ ገብሩ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋዩ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ ፤
በእንተ ነፍሰ ገብሩ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋዩ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ ፤
ወበእንተ ኵሎሙ እለ ዝየ ሀለዉ ዘአንተ ጸዋዕከ እምውስተ ሕዝብከ በጽድቅ ወበርትዕ ሕፅን ነፍሶሙ ውስተ መካን ሥዑር ወኀበ ማየ ዕረፍት ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ፤	ከወገኖችህ ለይተህ በእውነትና በሚገባ ስለ ጠራሃቸው በዚህ ቦታ ስላሉ ሰዎችም ሁሉ በለመለመ ቦታ በዕረፍት ውኃ ዘንድ፣ በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብም አጠገብ ነፍሳቸውን አሳርፍ ፤
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፤
ዘለዕረፍት ሥልጣን ብከ እግዚአብሔር አምላክነ፤	ዕረፍትን ለመስጠት ሥልጣን ያለህ አምላካችን እግዚአብሔር አንተ ነህ ፤
ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ እለ ኖሙ፣ አበዊነ ጳጳሳት፣ ወአበዊነ ኤጲስቆጶሳት፣ ወአበዊነ ቀሳውስት ወአኃዊነ ዲያቆናት፣ ወአበዊነ መነኮሳት፣ ወአኃዊነ ሕዝባውያን ፤ ወአኃቲነ አንስት፣ ከመ ያዕርፍ እግዚእ ነፍሳቲሆሙ በሰማያት ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ፣	ይ.ዲ. ጸልዩ፣ ስለ ሞቱት አባቶቻችን የጳጳሳት አለቆችና ስለ አባቶቻችን ጳጳሳት ፤ ስለ አባቶቻችን ኤጲስቆጶሳት ፤ ስለ አባቶቻችን ቀሳውስት፣ ስለ ወንድሞቻችን ዲያቆናት፣ ስለ አባቶቻችን መነኮሳት ፤ ወንድሞቻችን ስለሆኑ ስለ ሕዝቡ ፤ እኅቶቻችንም ስለሆኑ ስለ ሴቶቹ ጸልዩ፣ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ነፍሳቸውን ያሳርፍ ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ፣

ግዕዝ	አማርኛ
ይ. ሕ. መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	ይ.ሕ. አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣
ይ. ካ. እግዚአብሔር አምላክነ ዘኵሉ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ በእንተ እለ ኖሙ አግብርቲከ ወአእማቲከ፣	ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ እግዚአብሔር ሆይ ስለ ሞቱት ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች አገልጋዮችህ እንለምንሃለን፤ እንማልድሃለን ፤
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፣
በእንተ ነፍሰ ገብርከ እጉነ ዕገሌ፣	ስለ አገልጋይህ ወንድማችን ስለ ዕገሌ ነፍስ እንለምንሃለን፤
ይ. ሕ. መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	ይ.ሕ. አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፣	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፣
መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ ገብርከ ዕገሌ፤	አቤቱ የአገልጋይህን የዕገሌን ነፍስ ማራት ፤
ይ. ካ. ወበእንተ ኵሎሙ እለ ዝየ ሀለዉ (ውስተ ዝንቱ መካን) ዘአንተ ጸዋዕከ እም ውስተ ሕዝብከ በጽድቅ ወበርትዕ አዕርፍ ነፍሶሙ ውስተ መካን ሥውር ወነበ ማየ ዕረፍት ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ በመራሕያነ ብርሃን መላእክቲከ ሕፅን ነፍሶሙ ምስለ ቅዱሳኒከ ውስተ ዘለዓለም ማኅደርከ፣ ወሥጋሆሙኒ አንሥእ በዕለተ ዐደምከ እንተ ባቲ ሠራዕከ በከመ ቅዱስ ወቡሩክ ዘኢይትሔሰው ተስፋከ፣	ይ.ካ. ከወገኖችህ ለይተህ አንተ በእውነት በሚገባ ጠርተሃቸው በዚሁ ቦታ ስለ አሉትም ሰዎች እንለምንሃለን፣ ነፍሳቸውን በለመለመ ቦታ በዕረፍት ውኃ ዘንድ በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብም አጠገብ በመንግሥተ ሰማያት አሳርፍ፣ ወደ ብርሃን በሚመሩ በመላእክትህ መሪነት በዘለዓለማዊት ማደሪያህ ውስጥ ነፍሳቸውን አሳድር ፣ ሥጋቸውንም ትንሣኤን በሠራህባት በቀጠሮህ ቀን አስነሣ የማይታበል ተስፋህ ቅዱስ ቡሩክ እንደመሆኑ መንግሥተ ሰማይን ዐድላቸው፣
ዘበሰማያት መንግሥተከ ክፍሎሙ፣ እስመ አልቦሙ ለአግብርቲከ ሞት አላ ፍልሰት ወለእመኒ ቦ ዘአበሱ ወዘተሠወሮሙ ሕገ ሰብእ አናኅሲ ሎሙ፣ እስመ ኄር ወመፍቀሬ ሰብእ አንተ እግዚአብሔር ፣ እስመ አልቦ ንጹሕ እምር ስሕት በቅድሜከ፣ ወለእመኒ ቦ አሐተ ሰዓተ ሐይዉ በዲበ ምድር ማኅለፍታተ ነፍሶሙ ግዑዘ ዘእንበለ ክልኣት አንተ ጸጉ፣ መንፈሰ ናዛዜ ወመናኅየ ለሰብአሙ ፈኑ፣ ናዝዞሙ ወአስ ተፍሥሖሙ፣	ለአገልጋዮችህ ከዚህ መሄድ እንጂ ሞት የለባቸውምና፣ በድለውም የተሠወራቸው ቢኖር ሰው እንደ መሆናቸው ይቅር በላቸው፣ ቸርና ሰውን ወዳጅ አንተ እግዚአብሔር ነህና፣ በፊትህ ከኃጢአት ንጹሕ የሆነ የለምና፣ በዚህ ዓለምስ እንኳ አንዲት ሰዓት ቢኖሩ የነፍሳቸውን መንገድ ያለ መከልከል አቅንተህ ስጥ ፣ የሚያረጋጋና የሚያሳርፍ መንፈስን ለሰዎቻቸው ላክ ፣
በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእጉዝ ይእዜኒ ወዘ ልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣	በክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል፣ ከርእሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ፣

ግዕዝ	አማርኛ
መስተብቍዕ ዘእግዝእትነ ማርያም ፣	የእመቤታችን የማርያም መስተብቍዕ፣
እግዚአብሔር እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነ ዘትቤሎ ለፍቁርከ ዮሐንስ እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ፣ ወትቤላ ለማርያም ነዋ ወልድኪ ወለረድእከኒ ነያ እምከ ወእምይእቲ ሰዓት ነሥኣ ውእቱ ረድእ ወአእተዋ ቤቶ፣ ይእዜኒ እግዚኦ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ በእንተ ማርያም ወላዲትከ ወበእንተ ዮሐንስ ዘረፈቀ ውስተ ሕፅንከ ወበእንተ ኵሎሙ ሐዋርያት አርዳኢከ ከመ ትረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ተአምሪሃ ለማርያም በእደዊሃ ዘከሠትከ፣	አቤቱ እግዚአብሔር አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በቅዱስ ዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ ለወዳጅህ ለዮሐንስ የነገርከው፣ ማርያምንም ይህ ልጅሽ ነው አልሃት፣ ከዚህችም ሰዓት በኋላ ይህ ደቀ መዝሙር ወሰዳት፣ ወደ ቤቱም አስገባት፣ አሁንም አቤቱ ስለ ወለደችህ ስለ ማርያም ብለን፣ በአጠገብህ ስለ ተቀመጠ ስለ ዮሐንስና ስለ ደቀ መዛሙርትህ ስለ ሐዋርያት ሁሉ ብለን እንለምንሃለን፣ እንማልድሃለን፣ በእጆችዋ የገለጽከውን የማርያምን ተአምር ለመስማት ታብቃን ዘንድ ፣
ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ፣	ይ.ዲ. ስለ ቅዱስ ወንጌል ጸልዩ ፣
ትእ. ለእመ ኮነ ምንባብ እምወንጌል ይበል ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ፣	ትእ. የሚነበበው ወንጌል ሲሆን በእንተ ወንጌል ቅዱስ ይባላል፣
ወለእመኮነ ምንባብ እምራእየ ዮሐንስ ይበል ጸልዩ በእንተ ተአምር ዘድንግል፣	ነገር ግን የሚነበበው ራእየ ዮሐንስ የሆነ እንደሆነ ጸልዩ በእንተ ተአምር ዘድንግል ይሏል ፣
ይ.ሕ. እግዝእትነ ተሣሃልነ ዘመንክር በአርያሙ እግዚአብሔር ስሙ ዝንጓጌ መስቀል አመ ተወፈየ ነዋ ወልድኪ ይቤላ ለእሙ፣ ፍቅረ ዮሐንስ ኢያንተገ በጊዜ ሕማሙ ላዕለ ጉንደ መስቀል አመ ውኅዘ ደሙ፣	ይሕ. እመቤታችን ሆይ ይቅር በዩን ፣ በአርያሙ የተደነቀው ስሙ እግዚአብሔር ነው፣ ደሙ በመስቀል ላይ በፈሰሰ ጊዜ በሕማሙ ጊዜም የዮሐንስን ፍቅር አላ ጎደለም፣
ይ. ዲ. እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ፣ ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ ፣ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም፣	ይ.ዲ. እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፣ ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶዋታልና፣ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ይህች ናት አለ ፣
ይ. ሕ. ከማሁ፣	ይ.ሕ. እንደርሱ ፣
ይ. ካ. ተዘከር ካዕበ እግዚኦ አግብርቲከ ወአእማቲከ እለ በልዑ ሥጋከ ወሰትዩ ደመከ ወእለ አዕረፉ በሃይማኖተ ዚአከ፣	ይ. ካ. አቤቱ ወንዶችና ሴቶችን አገልጋዮችህን ሥጋህን የበሉትን ደምህንም የጠጡትን፣ በሃይማኖት የሞቱትን አስብ፣
ኦ በግዕ ዘአርያም በርእሰ ደብረ ጽዮን ዘቆምከ ኢትፍልጠነ እምከብካበ ቅዱስ መርዓከ ኢተዘኪረከ አበሳነ ወአናኅስየከ ጌጋየነ በምሕረትከ ተዘከረነ፣ እንበለ ምሕረትከሰ ኀልቦ ዘይድኅን ፣	በጽዮን ተራራ ራስ የቆምህ በግዕ ሆይ፣ ከሙሽርነትህ ሠርግ አትለየን፣ በደላችንን ሳታስብ ኃጢአታችንን አቃለህ በቸርነትህ አስበን ፣ ያለምሕረትህ ግን የሚድን የለም፣

ግዕዝ	አማርኛ
ለከ ይደሉ ስብሐት በጽዮን ወለከ ይትፌኖ ጸሎት በኢየሩሳሌም ስማዕ ጸሎተ ኵሉ ዘሥጋ በእንተ ማርያም ምልዕተ ጸጋ ይእዜኒ ወዘ ልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፣ ይ. ሕ. አሜን ፡፡	በጽዮን ለአንተ ምስጋና ይገባል፣ በኢየሩሳሌምም ለአንተ ምስጋና ይላካል፣ የሥጋውያንን ሁሉ ጸሎት ጸጋን ስለ ተመላች ስለ ማርያም ብለህ ስማ ፣ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ፤ ይ.ሕ. አሜን ፡፡
ዓዲ	ዓዲ (ዳግመኛ)
ይ.ካ. ወካዕበ ናስተበቍዓ ለንግሥተ ኵልነ ማርያም እምነ ወእሙ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ንስእል ወነኃሥሥ ናስተ በቍዕ ወንዋድስ ዕበየ ተአምራቲሃ ብዙኃ ለእመ ጸባዖት ንጉሥ፣ እለ ትነብሩ ተንሥኡ ወእለታረምሙ አውሥኡ ማርያምሃ በቃለ ስብሐት ጸውዑ ቁሙ ወአጽምዑ ተአምረ ድንግል ከመ ትስምዑ፣ ይ.ዲ. ጸልዩ ቅድመ ሥዕላ ለቅድስት ድንግል መርዓተ አብ ወእመ በግዑ፣ ይ.ሕ. ቡርክት አንቲ ማርያም፣ ውድስት አንቲ ማርያም፣ ሠናይት አንቲ ማርያም፣ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ መድኃኔ ኵሉ ዓለም፣ ይ.ካ. ንዑ ንስግድ ወንግነይ ላቲ ንዑ ንትፈሣሕ ወንትጎሠይ ባቲ እስመ እመ አምላክ ይእቲ ድንግልናቲሃ ፪ቲ፣ ዛቲ ይእቲ ትንቢቶሙ ለነቢያት ሞገሰ ስብከቶሙ ለሐዋ ርያት እሞሙ ለሰማዕት ወእኁቶሙ ለመላእክት ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወለወልዳ አምልኮ ወስግደት በምድር ወበሰማያት በባሕር ወበቀላያት ለዓለመ ዓለም ፤ ይ.ሕ. አሜን፡፡	ይ.ካ. የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናትና እናታችን የሁላችን ንግሥት ማርያምን ዳግመኛ እንማል ዳታለን፣ የአሸናፊ ንጉሥ እናት የተአምራቶቿን ገናንነት እናመሰግናለን እንማልዳለንም፤ የተቀመጣችሁ ተነሡ የማታመሰግኑ አመስግኑ ማርያምን በምስጋና ቃል ጥሯት፣ የድንግልን ተአምር ትሰሙ ዘንድ (እንድትሰሙ) ቁማችሁ አድምጡ፤ ይ.ዲ. በአብ መርዓት ፣ በወልድ እናት፣ በቅድስት ድንግል ሥዕል ፊት ጸልዩ፣ ይ.ሕ. አንቺ ማርያም ሆይ የተባረክሽ ነሽ፤ አንቺ ማርያም ሆይ የተመሰገንሽ ነሽ ፣ አንቺ ማርያም ሆይ ያማርሽ ነሽ ፣ የማኅፀንሽም ፍሬ መድኃኔ ዓለም የተባረከ ነው፣ ይ.ካ. ኑ እንስገድ እንገዛላትም ኑ እንደሰት እንደሰትባትም በሁለት ወገን ድንግል ስትሆን የአምላክ እናት እርስዋ ናትና፣ የመላእክት እኅት፣ የሰማዕታት እናት፣ የሐዋርያት የስብከታቸው ደስታ፣ የነቢያት ትንቢት እርሷ ናት፣ ለእርሷ ክብርና ምስጋና ይገባል፣ ለልጇም በሐይቆችና በበባሕር በሰማይና በምድር ማመንና ስግደት ይገባል ለዘለዓለሙ ይ. ሕ. አሜን፡፡

ግዕዝ	አማርኛ
መስተብቍዕ ዘመስቀል	**የመስቀል መስተብቍዕ**
ይ.ካ. ወካዕበ ናስተበቍዖ ለዕፀ ቅዱስ መስቀል ጽኑዐ ሥልጣን ወኃይል ወሊሉየ መልክዕ ወአካል፣ እመልክዐ በትሩ ለአሮን ካህነ ጽላሎት ወአምሳል፣ በትረ አሮንሰ ዘሠረፀት ወፈረየት ከርካዐ ዘእንበለ ተክል ፣ እንዘ ትቀውም በአፍኣ፣ ኢያድኅነት ጻድቀ ወኢቤዘወት ኃጥአ ፣ እስመ አልባቲ ክሂል ወኢመዊዐ ፣ መስቀለ ክርስቶስሰ ቤዛነ ወኃይልነ አግዓዘ ጻድቃነ ወኃጥአነ እምግብርናተ ሰይጣን ጸላኢነ ሚአ ሥልጣነ እምኀበ እግዚአብሔር ኃምላክነ ፣	ይ.ካ. በመልክና በአካል ከጥላና ከምሳሌ ካህን አሮን በትር መልክ የተለየ መልክ ያለው በኃይልና በሥልጣንም የጸና የሆነ የተቀደሰ ዕፀ መስቀልን ዳግመኛ እንማልደ ዋለን፣ በውጭ ቆማ ሳለች ሳይተክሏት የበቀለችውና ሎሚን ያፈራችው የአሮን በትርስ ጻድቅንና ኃጥእን ፈጽማ አላዳነችም፣ የማዳን ችሎታ የላትምና፣ ቤዛችንና ኃይላችን የሆነው የክርስቶስ መስቀል ግን ከእግዚ አብሔር አምላካችን ሥልጣንን ተቀብሎ ከሰይጣን ጠላታችን ባርነት ጻድቃንንና ኃጥ አንን ነጻ አወጣ፣
ይ. ዲ. ጸልዩ ቅድመ መስቀል ኵልክሙ ሠላይምናን እንዘ ትእኀዝዎ በየማን ወትክ ሐድዎ ለሰይጣን እስመ ተቀደሰ በደመ ክርስቶስ መድኀን፣	ይ. ዲ. ሁላችሁ መኃይምናን ሆይ ሰይጣንን እየካዳችሁ መስቀልን በቀኝ እጃችሁ እየያዛ ችሁ በመስቀል ፊት ጸልዩ በመድኃኒታችን ክርስቶስ ደም ተቀድሷልና፣
ይ.ሕ. ክቡር አንተ ንጉሠ ዕፀዋት መስቀል፣ ክቡር አንተ ዕፀ መስቀል ወክቡር ዘተቀደስከ ደመ ክርስቶስ ቃል፣	ይ.ሕ. አንተ የዕፀዋት ንጉሥ መስቀል ክቡር ነህ፣ ክቡር የሆንክ አንተ ዕፀ መስቀል በክርስቶስ ቃል ደምም የተቀደስክ ክቡር ነህ፣
ይ.ካ. ለክብረ ዝንቱ መስቀል ክርስቶሳውያን ስግድ በፍርሃት ወበረዓድ ኪያሁ ፈጣሪ ሰዊ ወልድ እስመ ቀደሶ በደሙ ወአኮ በደመ ፍየል፣ በመልዕልተ ዝንቱ መስቀል አመ ሞተ ሞለኮት በትስብእቱ ትሰብእትሰ እመለኮቱ ተፈልጠ ወኢተቆስሐ ቦቱ፣	ይ.ካ. ክርስቲያን ሆይ ለዚህ መስቀል ክብር በመፍራትና በመንቀጥቀጥ እንስገድለት፣ ፈጣሪ በሌላ ደም ያይደለ በራሱ ደም እርሱን ቀድሶታልና፣ መለኮት በትስብእት በዚህ መስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ትስብእትም ከመለኮት አልተለየም፣ የተጨመረበትም የለም፣
በትረ ዝንቱ መስቀል ሐዋርያቲሁ ወሞተ እንዘ ይገብሩ መንክራተ ፣ ሰደዱ ሠንሠለተ ወሰበሩ ጣዖታተ፣ በእንተ ዝንቱ አዘዙ ሥምሀራነ ቅዱስ ወንጌል ፣ አምሳለ ፈጣሪ ዓለል ፣ ንስግድ ለመስቀል ወለማርያም ንግል፣ ለማርያምሰ ዘንሰግድ ላቲ እስመ ሠአ ሥጋ እምሥጋሃ እግዚአብሔር ባሪሃ፣	የሞተው ክርስቶስ ደቀ መዛሙርትም በዚህ መስቀል በትር ተአምራትን እያደረጉ አጋንንትን አባረዋል ፣ ጣዖታትንም ሰባብረ ዋል፣ ስለዚህ የቅዱስ ወንጌል መምህራን ለልዑል ፈጣሪያችን የባሕርይ ስግደት እንዲገባ ለመስቀልና ለድንግል ማርያምም የጸጋ ስግደት እንሰግድላቸው ዘንድ አዝዘው ናል፣ ለማርያም የምንሰግድላት ፈጣሪዋ እግዚ አብሔር ከሥጋዋ ሥጋን ስለነሣ ነው፣ እኛም ከእርሷ መድኃኒትን ስለአገኘን ነው፣

ዕዮሄዕ

ግዕዝ	አማርኛ
ወረከብነ ንሕነ መድኃኒተ እምኔሃ ፣ ለዕፀ መስቀልኒ ከመ ተናገርነ ቅድመ በላዕሌሁ አንጠብጠበ ደመ፣ ቃል ኢሐማሚ በባሕርየ ሥጋ ዘሐመ፣ ለእሉ ፪ቱ ፍጡራን ሰብሐት ይደልዎሙ እስመ ተዐረዩ በክብሮሙ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም ፤	አስቀድመን እንደተናገርነው ለዕፀ መስቀልም የምንሰገድለት በሥጋ ባሕርይ የታመመው በመለኮት ያልታመመው የቃል (የክርስቶስ) ደም በላዩ ስለፈሰሰበት ነው፣ ለእነዚህ ሁለት ፍጡራን የጸጋ ምስጋና ይገባቸዋል፣ በክብር ተስተካክለዋልና ዛሬም ዘወትርም ለዘለ ዓለሙ፤
ይ.ሕ. አሜን፡፡	ይ.ሕ. አሜን፡፡